## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን

# የ2018 በጀት ዓመት የ6 ወራት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት

ታህሳስ 30 /2018 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


1. መግቢያ ....... 3
የኢትዮጵያ ግብርና ባልስለጣን የ2018 በጀት አመት የ6 ወራት ክንውን ....... 4
2. የዕጽዋት ምርትና ግብዓት ጥራት ቁጥጥር ዘርፍ ....... 4
2.1 ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ ....... 4
2.2 ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች ....... 4
2.3 በላቦራቶሪ የጥራት ፍተሻ የተደረገላቸው የ ዕጽዋት ዘር፣ ምርትና የ ዕጽዋት ውጤቶች ....... 7
2.4 የዕጽዋት ዝርያ ጥበቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር ....... 8
2.5 የተጠናከረ የህግ ማዕቀፍ ተፈጻሚነት አቅም ግንባታ እና ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት ....... 10
3. የእንስሳት ምርትና ግብዓት ቁጥጥር ዘርፍ ....... 17
3.1 የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ ....... 17
3.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ....... 21
3.3 ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት ....... 23
✓ የእንስሳት መድኃኒት ጥራት ፈዋሽነትና ደህንነት ማረጋገጥ ....... 27
3.4 ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ ....... 28
✓ የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነትን ማረጋገጥ ....... 32
3.5 ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የዕጽዋት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት ....... 33
የመረጃ አቅርቦት ሥርዓት እና አጠቃቀምን ማሻሻል ....... 36
የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት ደረጃ ማሳደግ እና ማሻሻሽል ....... 37
የአመራርና ፈጻሚ አካላት አቅም መገንባት ....... 38
ድጋፍ ማፈላለግ እና የሃብት ምንጭ ማሳደግ/ማበራከት ....... 40
ቅንጅታዊ አሰራርን ማሻሻል እና ማጠናከር ....... 41
የማዕከሉን ክትትልና ግምገማ፣የድጋፍና ግብረ መልስ አሰራርን ማጎልበት ....... 42
4ታቅደው ያልተከናወኑ ሥራዎች ከነምክንያታቸው ....... 42
5ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ....... 43

ተቋማዊ ለውጥ ሥራዎች ማሳደግ ........ 53
አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት ........ 59
6. የበጀት አጠቃቀም ........ 61
7. ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍ ........ 62
8. በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች፣ የተወሰዱ እርምጃዎች እና በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገቡ መፍትሄዎች ........ 64
የተወሰዱ እርምጃዎች እና በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገቡ መፍትሄዎች ........ 65

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ10 ዓመትና የመካከለኛ ዘመን የግብርና ሴክተር ዕቅድ አካል የሆነውን የግብርና ሬጉላቶሪ ዕቅድ መሠረት በማድረግ የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ ክንወን አምርቂ ውጤቶችን በማስመዝገብ አጠናቋል፡፡ ባለፉት 6 ወራት ከተከናወኑ አብየት ክንውኖች መካከልም ከተለይእዩ ባልድርሻ ኣአካላት ጋር የተደረጉ ቅንጀታዊ አሰራሮች የትብብር ስምምንቶች ለክልል ባለድርሻ አካላት  የተደረጉ የቴክኒክና የስልጠና ድጋፎቸ፣የዳሰሳ ጥናቶች ዋናውን ድርሻ የያዙ ሲሆን በጸቀዱ መሰረትም የግብርና ሬጉላቶሪ ስራዎችን የሚያጠናክሩ የዲጂታላየዜሽን ስራዎችን አጠናክሮ ማሰቀጠል ተችሏል፡፡ በስትራቴጂክ ዕቅዱም በዋናና ልዩ የትኩረት መስክነት የተያዙ፣ እንደ ዲጂታይዜሽን ፣የህግ ማዕቀፍ ማሻሻያ ስራዎችን ታሳቢ ያደረገና ባለው የሰው ሀይልና ሌሎች ሀብቶች ተጠቅሞ የተከናወነ ሪፖርት አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡

በስትራቴጂክ ዕቅዱም በዋናና ልዩ የትኩረት መስክነት የተያዙ፣ እንደ ዲጂታይዜሽን ፣ የህግ ማዕቀፍ ማሻሻያ ስራዎችን ታሳቢ ያደረገና ባለው የሰው ሀይልና ሌሎች ሀብቶች ተጠቅሞ የተከናወነ ሪፖርት አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡

# የኢትዮጵያ ግብርና ባልስለጣን የ2018 በጀት አመት የ6 ወራት ክንውን

## 2. የዕጽዋት ምርትና ግብዓት ጥራት ቁጥጥር ዘርፍ

### 2.1 ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ

- ✓ ባለፉት ስድስት ወራት የ69299 ቶን ፀረ ተባይ ፍቱንነት፣ደህንነትና ጥራትን የማረጋገጥ ስራ ለማከነወን ታቅዶ የ 60287 ቶን የፀረ ተባይ ፀረ ተባይ ፍቱንነቱ፣ ደህነነቱ እና ጥራቱን ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ሲሆን ይህም አፈጻጸሙ 87.14% ነው::
- ✓ ባለፉት ስድስት ወራት 854649 ቶን የአፈር ማዳበሪያ ፣ደህንነትና ጥራትን የማረጋገጥ ስራ ለማከነወን ታቅዶ የ 542091 ቶን የአፈር ማዳበሪያ ፣ ደህነነቱ እና ጥራቱን ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ሲሆን ይህም አፈጻጸሙ 63.43% ነው::
- ✓ ባለፉት ስድስት ወራት ለ180 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ168 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠ ሲሆን ይህም አፈጻጸሙ ከ93.33% ነው::
- ✓ ባለፉት ስድስት ወራት በአካባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋት ለመቀነስ የሚያስችል 2 የዳሰሳ ጥናት ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 2 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 100 ነው::
- ✓ ባለፉት ስድስት ወራት በመስክ ምርምር ፣ በዶዜር ግምገማ እና በቤተ-ሙከራ ፍቱንነቱ፣ ደህንነቱ ና ጥራቱ ተረጋግጦ ለ235 ፀረ-ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ምዝገባ ለማከናወን ታቅዶ 317 ተከናውናል አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው::

### 2.2 ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች

#### 2.2.1 ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች

- ባለፉት ስድስት ወራት ወደ ዉጪ ሀገር በሚላክ 480,000 ቶን የጥራጥሬ፣ የቅባት፣ የብርና አገዳ እህሎች፣ የቡና፣ የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ቅመማቅመም ምርት እንዲሁም ሌሎች የግብርና ምርቶች ላይ ተገቢውን ምርመራ ወይንም ኢንስፔክሽን

ለማካሄድ ታቅዶ 422,755 (88%) ምርትላይ ምርመራው ተክናውኖ ወደ ተለያዩ ሃገራት እንዲላክ ተደርጓል፡፡

### 2.2.2 ጤንነቱ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች፣

- ባለፉት 6 ወራት በ32,500 ቶን ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ዉጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሶች ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ ለመስራት ታቅዶ በ123,704 (>100 %) ቶን ላይ የኢንስፔክሽን ሥራዎችን በማከናወን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነው በዚህ ሩብ ዓመት የዛላ በርበሬ፣ ቅመማቅመም ምርት እና ለርዳታ የገባ የማሽላ ምርት በመጨመሩ ነው፡፡የኣአፈጻጸም ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ወደ ውጪ ለሚወጣ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶችና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች የማጠንት /Fumigation ህክምና ሲካሄድ ክትትል ለማድረግ በዚህ 6 ወር 200,000 ቶን ታቅዶ ክንዉን 116,223 ቶን (58%) ምርት ከተባይ ነፃ በማድረግ ወደ ተለያዩ ሃገራት መላክ ተችሏል፡፡ ለአፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን በዚህ ሩብ ዓመት ውስጥ በተቀባይ ሀገሮች ምርቱ ታጥኖ እንዲላክ የተቀረበ ጥያቄ አናሳ መሆኑ::
- ወደ ውጪ ለሚወጣ የዕፅዋት የጤንነት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት በዚህ 6 ወር በቁጥር 30,000 ለመስጠት ታቅዶ ክንዉን 26,405 (88%) ለማሳካት ተችሏል፡፡
- በዚህ 6 ወር ወደ ውጭ በሚላኩ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች ላይ 99% ተቀባይነት ያለው እና የተቀባይ ሀገር ቅሬታን (Notification) ለመቀነስ ታቅዶ 97% ተቀባይነት ያገኘ ምርት መላክ ተችላል ::
- በዚህ ሩብ ዓመት 15 የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎችን ላይ የመስክ ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ 15 (100%) ላይ ሙያዊ ድጋፍ መስጠት ተችሏል:
- በዚህ 6 ወር ወደ አውሮፓ ህብረት በሚላኩ የሮዝ አበባ አምራች ላኪዎች በተቀመጠው FCM መቆጣጠሪያ ሰነድ /System approch document/ መሰረት መስራታቸውን በአውሮፓ ኦዲተሮች ብሔራዊ የዕፅዋት ጥበቃ ድርጅት/NPPO/ ኦዲት ተደርጓል ::
- በዚህ 6 ወር ወደ አሜሪካ የሚላክ የአበባ ቁረጥራጭ/Pelargonium/ እርሻዎች ምርታቸው ከ Ralstonia ከተባለ ባክቴሪያ ነጻ መሆኑን በአሜሪካ ኦዲተሮች በተካሄደው ኦዲት ውጤት እንደ ሀገር ማለፍ ችለናል::
- በዚህ ሩብ ዓመት ወደ አውሮፓ የሮዝ አበባ ምርት የሚልኩ አምራች ላኪዎች በምርት ተቀባይ ሀገር እርሻዎች እና የስራ ክፍሉ የFCM መቆጣጠሪያ ሰነድን /System approch document መተግበሩን በአውሮፓ ሕብረት ኦዲተሮች ኦዲት እንዲደረግ ዝግጅት እና

ክትትል ተደርጓል::

- ከእርሻዎችና ከሌሎች አካባቢዎች የተሰበሰቡ ናሙናዎች በላብራቶሪ ተመርመረው ኢትዮጵያ ከXylella Fastidoisa ባክቴሪያ ነፃ መሆኗ ተረጋግጦ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ተልኳል።
- ለዕፅዋትና ዕፅዋት ዉጤቶች ተቀባይ ሀገር የተባይ ስጋት ትንተና ቴክኒካል መረጃ/ሰነድ ለመላክ በዚህ 6 ወር በቁጥር 3 መረጃ ለመስጠት ታቅዶ ለስራ ክፍሉ በቀረበው አንድ መጠይቅ ላይ መረጃ በማሰባሰብ ለሚመለከተው አካል ተለኳል::

2.2.3 ባለፉት 6 ወራት በቁጥር 1,000 ገቢ ዕፅዋትና፣ የዕፅዋት ውጤቶች፣ እንዲሁም ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች የመግቢያ መስፈርቶችን አሟልተው ስለመግባታቸው ለማረጋግጥ ታቅዶ በ1,045 (>100%) የማረጋገጫ ስራ ተሰርቶ የቅድመ ማስገቢያ ፍቃድ ተሰጥቷል።

- በገቢ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶች፣ ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶችና ላይ የመግቢያ መስፈርቶችን አሟልተው እንዲገቡ በዚህ 6 ወር በቁጥር 1,000 በዕቅድ ተይዞ 1,045 (>100%) የቅድመ ማስገቢያ ፍቃድ ተሰጥቷል።
- ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ዉጤቶች እና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች የሚገቡባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኃላ የጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ በዚህ 6 ወር በቁጥር 950 ለመስጠት ታቅዶ ክንውን 628 (66%) መስጠት ተችሏል:: ለአፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን በአንድ የማስገቢያ ፈቃድ ላይ የሚጠየቀው መጠን መብዛት ነው።
- በዚህ 6 ወር ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ 2000 ቶን ታቅዶ 290 ቶን ላይ ምርመራ ተደርጎ እንዲገባ ተደርጎዋል።
- በዚህ 6 ወር በድህረ መግባት ኳራንቲን (Post Entry Quarantine) ማለፍ ያለባቸውን ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች ክትትል ለማድረግ 3 ታቅዶ 3 (100%) መስጠት ተችሏል::
- በዚህ 6 ወር ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ዕፅዋትና የዕፅዋት ዉጤቶች የተባይ ስጋት ትንተና የመስክ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ 2 ታቅዶ ክንውን 2 (100%) ላይ መስራት ተችሏል::
- ለዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች የጥራት እና ደህንነት የደረጃዎች ዝግጅት ማካሄድ በዚህ 6 ወር 2 ታቅዶ 2(100%)።

2.2.4 **የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች**

- ባለፉት 6 ወራት በቁጥር 340 ለሚሆኑ አዲስ እና እድሳት የሚፈልጉ ገቢና ወጪ የዕፅዋት ምርቶች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ 170 (50%)

መስጠት ተችሏል :: አፈጻጽሙ ዝቅተኛ የሆነው ለስራ ክፍሉ የቀረቡት የብቃት ማረጋገጫ እድሳት ጥያቄዎች ዝቅተኛ መሆንና በተለይም አስመጪዎች የስራ ዘርፍ መቀየር፣ ለአንድ ጊዜ ብቻ ብቃት ማረጋገጫ መውሰድና በዘርፉ አለመቀጠል የእድሳት ቁጥር እንዲቀንስ አድርጎታል፡፡ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በዚህ 6 ወር በገቢና ወጭ የግብርና ምርቶች ላይ የብቃት ማረጋገጫ ለሚጠይቁ ተገልጋዮች የባለሙያ፣ የቢሮ፣ የመጋዘን ኢንስፔክሽን በማካሄድ እና ሌሎች መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸው በማረጋገጥ በቁጥር 100 ለመስጠት ታቅዶ 101 (>100%) አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስጠት ተችሏል፡፡
- በዚህ 6 ወር ከስራ ክፍሉ የብቃት ማረጋገጫ ስርተፊኬት ለተሰጣቸው ድርጅቶች/ግለሰቦች ተገቢውን የቢሮና የመጋዘን ኢንስፔክሽን ማድረግ በቁጥር 240 ለማደስ ታቅዶ 69 (29 %) ድርጅቶች/ግለሰቦች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስጠት ተችሏል፡፡ለአፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን በዚህ ሩብ ዓመት ለስራ ክፍሉ የቀረቡ የእድሳት የአመልካች ቁጥር መቀነስ ነው፡፡
- ለዕፅዋት ምርት አስመጭነትና ላኪነት ብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ድርጅቶች/ግለሰቦች በመስፈርቱ መሰረት እየሰሩ መሆናቸዉን ክትትልና ግምገማ ለመድረግ በቁጥር 20 ታቅዶ 20 (100%) ላይ ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡

## 2.3 በላቦራቶሪ የጥራት ፍተሻ የተደረገላቸው የ ዕጽዋት ዘር፣ ምርትና የ ዕጽዋት ውጤቶች

- ✓ ባለፉት 6 ወራት በ140 የተለያዩ የአትክልትና የሰብል ዘር ናሙናዎች ላይ የላብራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ ለማከናወን እና ውጤት ለማሳወቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን በሩብ ዓመቱ ለጥራት ፍተሻ ላቦራቶሪው የቀረበው የናሙና ብዛት መጠን ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በ6 ወሩ በ163 የተለያዩ የአትክልትና የሰብል ናሙናዎች ላይ የጥራት ፍተሻ ስራ ተከናውኗል፡፡
- ✓ በ6 ወር ውስጥ ከክልል በሚመጡ በ20 የተለያዩ የሰብል/የአትክልት ዱፕሊኬት (Duplicate) ናሙናዎች ላይ የንጽጽር የላብራቶሪ ፍተሻ ስራዎች ለማከናወን ታቀዶ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን ለጥራት ፍተሻ ላቦራሪው የመጣው እና የንጽጽር የላብራቶሪ ፍተሻ የተሰራው በ18 ናሙናዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ ይህም አፈጻጸም በመቶኛ 90% ነው፡፡ የናሙና መጠን የቀነሰበት ምክንያት የአንድ የክልል ላቦራቶሪ ናሙና ዘግይቶ ላቦራቶሪያችን በመድረሱ ነው፡፡

✓

## 2.4 የዕጽዋት ዝርያ ጥበቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር

### 1. የዝርያ ምዝገባና የዘር ጥራት ቁጥጥር ቅልጥፍናና ጥራትን ማሳደግ፣

- ✓ ከተለያዩ የምርምር ተቋሞች፣ ዩንቨርሲቲዎች እና የግል ኩባንያዎች የቀረቡ 70 ዕጩ ዝርያዎችን በዚህ ሩብ ዓመት ውስጥ በመስክ ግምገማ ለማካሄድ ታቅዶ 75 ዝርያዎች (107%) በመስክ ተገምግመዋል፡፡

| ተ.ቁ | የሰብል ዓይነት | የተገመገሙ ዝርያዎች ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | የብርዕ እና አገዳ ሰብሎች | 16 |
| 2 | የአትክልት ሰብሎች | 35 |
| 3 | የጥራጥሬ ሰብሎች | 11 |
| 4 | የቅባት ሰብሎች | 8 |
| 5 | የመኖ ሰብሎች | 4 |
| 6 | የኢንዱስትሪ ግበዓት ሰብሎች | 1 |
| ድምር | | **75** |

**በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ የአገር ውስጥ ዘር**

- ✓ እስከዚህ ሩብ ዓመት የአትክልት ዝርያዎችን ከውጪ በማስገባት ለአርሶአደሩ ለማቅረብ ጥያቄ ለሚያቀርቡ 15 የአትክልት ዘር አስመጪዎች አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ አዲስ 14 (93.3%) እድሳት 22 በድምሩ 36 ተከናውኗል፡
- ✓ **በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ ከውጭ አገር የገባ ዘር መጠን ውስጥ ለላብራቶሪ የቀረበ የናሙና ብዛት**

  **በ (ISTA) ስታንደርድ መሰረት ከተለያዩ የዘር አስመጭዎች** 140 **የዘር ናሙናዎችን በመውሰድ የጥራት ምርመራ እንዲከናወን ለላብራቶሪ ለማቀረብ** ታቅዶ 163 (116%) ተከናውኗል፡፡ ከውጪ ሀገር ገብቶ ለላብራቶሪ ፍተሻ የቀረበው ናሙና የሚወክለው የዘር (የአትክልት ዘር) መጠን 214,992 ኪ.ግ ነው፡፡

## 2018 ለላብራቶሪ ፍተሻ የተወሰደ ናሙና ብዛት ዝርዝር በሰብል ዓይነት

| No | የአትክልት ዘር | የተሰበሰበ ናሙና ብዛት | መጠኑ በኪግ |
|---|---|---|---|
| 1 | ቀይ ስር | 14 | 29,404.25 |
| 2 | ጥቅል ጎመን | 27 | 25, 644.98 |
| 3 | ሽንኩርት | 50 | 115,575.543 |
| 4 | ቲማቲም | 18 | 4,485.41 |
| 5 | ካሮት | 16 | 24,137.5 |
| 6 | ቆስጣ | 14 | 13,345.31 |
| 7 | ሰላጣ | 4 | 1,448 |
| 8 | ሀብሀብ | 8 | 7,328 |
| 9 | ብሮኮሊ | 4 | 103 |
| 10 | Squash | 1 | 7 |
| 11 | ቃሪያ | 2 | 18.5 |
| 12 | አበባ ጎመን | 2 | 50 |
| 13 | Spinach | 2 | 984.25 |
| 14 | Cucumber | 1 | 100 |
| **Total** | **163** | **222,631.743** | |
| | | | |
| | | | |

## 2. የአገልግሎት ክፍያ አሰባሰብ ሥርዓት ማጠናከር፣

- ለዘር ጥራት ቁጥጥሩ ለሚሰጠው አገልግሎት በክፍያ ደንቡ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል በመሆኑም በስድስት ወር ውስጥ 15,000ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 24,521 (>100%) ብር ተሰብስቧል፡፡

## 2.5 የተጠናከረ የህግ ማዕቀፍ ተፈጻሚነት አቅም ግንባታ እና ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት

### 2.5.1 የተጠናከረ የህግ ማዕቀፍ

***ፀረ ተባይና ማዳበሪያ ሪጉላቶሪ ሥሪ አስፈጻሚ***

- *የማዳበሪያ እና የአፈር ለምነትና ጤንነት ማሻሻያ ግብዓት አቅርቦት ፣ አጠቃቀም እና ቁጥጥር አዋጅ ከተለያዩተቋማት የተውጣጡ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ከኤቲአይ ጋር በመተባበር በድጋሜ የማሻሻል ስራ ተሰርቷል፡፡*
- *በጸረ-ተባይ ግምገማና ቁጥጥር አዋጅ* 674/2002 *ለመከለስ እንዲቻል ሰፊ ሀገር-አቀፍ ጥናት ተደርጎ ፥ጥናቱ በባለድሻ አካላት ቀርቦ እና ግብረ-መልስ ተሰብስቦ ፥የማሻሻያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ እና ለባለድርሻ አካላት ውይይት ቀርቦ ገንቢ አስተያቶችበመሰብሰብ ወደ ግብርና ሚኒስቴር ለመላክ የቅድመ-ዝግጅት ስራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡*
- *ለአዲሱየጸረ-ተባይ ምዝገባ መመሪያ መተግበር አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንካስመዝጋቢዎች ለማሰባሰብ በመስሪያ ቤቱ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለሶስት ተካታታይ ጊዜያት እና በመጨረሻም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመጨረሻ ማስታወቂያ እንዲወጣ በማድረግና እና ከዚሁ ጎን ለጎን ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሁለት ዙር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናከተሰጠ በኃላሙሉ ለሙሉ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡*
- *የጸረ-ተባይ ኢንስፔክሽን የተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ረቂቅ መመሪያ እና የስነ-ሕይወታዊ ጸረ-ተባይ እና የመከላከያ አካላት የምዝገባ መመሪያየፌድራል አስተዳደርና ስነ-ስርዓት አዋጅን* 1183/2012 *ድንጋጌን መከተልሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ በማስተዋወቅናለባለድርሻ አካላት ውይይት በማቅረብ ገንቢ አስተያቶችበመሰብሰብ ወደ ግብርና ሚኒስቴር ለመላክ የቅድመ-ዝግጅት ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡*

***እፀዋት ኳራንቲን ሪጉላቶሪ መሪ ሥራ አስፈጻሚ***

- *ረቂቅ የዕፅዋት ጥበቃና የኳራንቲን አዋጅ በግብርና ፣ሚ ኮሚቴ እና ባለድርሻ አካል የተሰጠውን አስተያየት በማካተት እንዲሁም በማስረዳት በዚህ ሩብ ዓመት አዋጁ እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡*
- *የዕፅዋት ምርት ጥራት እና ደህንነት ዜሮ ድራፍት አዋጅ እና ጥናታዊ መነሻ ፅሑፍ*

ተዘጋጅቶ ለህግ ክፍል እና ለመስሪያቤቱ ጽ/ቤት ሃላፊ ቀረቧል፡፡

- በዚህ 6 ወር የ Local Ethio-GAP ዶክመንት ተጠናቆ ቫሊዴት ተደርጓል፡፡
- በዚህ 6 ወር በበጀት ዓመቱ በስራ ክፍሉ የሚዘጋጁ የህግ ማህቀፎች ተለይተው ለህግ ክፍል ተልኳል፡፡
- በዚህ 6 ወር የተዘጋጀውን የዕፅዋት ተባይ ትንተና እና አሰሳ/PRA/ ጥናታዊ መረጃዎችን እንዲታተሙ ክትትል ተደርጓል፡፡
- በዚህ 6 ወር PRA operational procedure የመጀመሪያ ድራፍት ተዘጋቷል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት የSystem approach Implementation and audit Procedure ተዘጋጅቷል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት የSystem approach Implementation internal Procedure ተዘጋጅቷል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት የSystems Inspection and Certification Standard Operating Procedures for Rose Flowers in Ethiopia ተዘጋጅቷል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት Risk Profiling Standard Operating Procedur ተዘጋጅቷል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት Export Inspection and Certification Standard Operation Procedure (SOP) እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት የካሳቫ ምርት ወደ ቻይና ለመላክ የስምምነት ሰነድ/Cassava Protocol/ ላይ አስተያየት ተሰቶ የመጨረሻው ሰነድ ለፊርማ ለሚመለከተው አካል ተልኳል፡፡
- ብሄራዊ የመልካም አመራረት ትግበራ በአትክልት እና ፍራፍሬ ሰብሎች ላይ ለመተግበር ቅድመ ዝግጅት እየተሰራ ይገኛል፡፡

**የዘር ጥራት ቁጥጥር ሪጉላቶሪ መሪ ሥራ አስፈጻሚ**

የዕጽዋት ዘር አዎጅ 1288/2015 መጽደቅን ተከትሎ መሻሻል ያለባቸው መመሪያዎች፡-

- መመሪያ ቁጥር 1065/2017 የዕጽዋት ዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ መመሪያ ጸድቋል
- መመሪያ ቁጥር 1097/2017 የዕፅዋት ዘር ሥራ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ እና አስተዳደር መመሪያ ጸድቋል
- መመሪያ ቁጥር 1098/2017 ጥራቱ የተገለጸ ዘር ማስፈጸሚያ መመሪያ ጸድቋል
- የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት የማያሟላ የዕጽዋት ዘር አጠቃቀም እና አወጋገድ መመሪያ ለማጽደቅ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ሲገኝ ለግብርና ሚንስቴር ማናጅመንት ለማቅብ ቀነ-ቀጠሮ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡

- ለራስ አገዝ እና ለሶስተኛ ወገን ዘር ጥራት ማረጋገጥ ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ ለማጽደቅ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ሲገኝ ለግብርና ሚንስቴር ማናጅመንት ለማቅብ ቀነ-ቀጠሮ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡
- ህገ-ወጥ የእጽዋት ዘር ግብይት ቁጥጥር መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቶና በመሚመለከታቸው አካላት ተከልሶ አስተያየቶች ተወስደዋል፣ ወደ ፍትህ ሚንስቴር ከመላኩ በፊት ለግብርና ሚንስቴር ለማቅረብ ቀነ ቀጠሮ እየተጠበቀ ነው፡፡
- የአገልግሎት ክፍያ ተመን ደንብ ዝግጅት የገንዘብ ሚንስቴር በተሰጠው አስተያየት መሰረት ማስተካከያ ተደርጎ ለገንዘብ ሚንስቴር በድጋሜ ተልኳል፡፡

### 2.5.2 **የተሰጠ አቅም ግንባታ ስልጠና**

**እፀዋት ኳራንትን ቁጥጥር መሪ ሥራ አስአጻሚ**

- ሁለት ባለሙያ በEAC የዕፅዋት ተባይ ስጋት ትንተና ስልጠና ላይ በመሳተፍ ስልጠና ወስደዋል፡፡
- የስራ ክፍሉ ሰራተኞች የ5 million data Encoder ሥልጠና እንዲወስዱ ክትትል ተደርጓል፡፡
- የስራ ክፍሉ ባለሙዎች እና የጣቢያ ኢንስፔክተሮች በCOLEAD e-learning Program በበየነ መረብ የሚሰጠውን ሥልጠና በመውሰድ እራሳቸውን በማብቃት የተለያዩ ሰርተፊኬቶችን ማግኘት ችለዋል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት በ TMA በጀት ድጋፍ በCABI ከፍተኛ ባለሙያዎች ለሥራ እና ለጣቢያ ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት 2 የዕፅዋት ተባይ ስጋት ትንተናና አሰሳ ዴስክ ላፊ እና ባለሙያ ለ5 ቀን ኬንያ በመሄድ ለስራ ክፍሉ የሚያግዙ ልምዶችን እንዲቀስሙ ተደርጎል፡፡
- በዚህ 6 ወር የስራ ክፍሉ ዴስክ ሃላፊ የተsሙን የሪፎረም ኮሚት አባል በመሆን አጠቃላይ የሪፎርም ስራዎችን እንዲሁም ለተsሙ ሰራተኞች በሪፎረሙ ዙሪያ ስልጠና መስጠት ላይ ተሳትፎ ተደርጎል፡፡

**የዝርያ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር ሥራ አስፈጻሚ የአቅም ግንባታ ስራዎች**

- በኢትዮጵያ/ፌደራል እና በኦሮሚያ ግበርና ምርምር ኢንስቲትዩት ስር ላሉ ለተመረጡ ተመራማሪዎች የጸደቀውን የእጽዋት ዝርያ ለቀቃና ምዝገባ መመሪያ 1065/2017 የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል፣

- በ "Climate Resilient Wheat Value Chain Development (CREW)" ፕሮጀክት ጋር በመነጋገር ፕሮጀክቱ ለሚያቅፋቸው ክልሎች ጋር የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ተስርቷል፣ ለሱማሌ ክልል ከግብርና፣ ከምርምር፣ ከዘር ኢንተርፕራይዝ ለተወጣጡ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች የዘር ጥራት ቁጥጥር ስራዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ጅጅጋ በመገኘት ተከናውኗል።
- ለኢትዮጵያ ዘር አሶሴሽን አባላት የዘር አዋጁን ተከትሎ ያሉ ለውጦች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል።

### 2.2.3 በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (Digitalization) የታገዘ አገልግሎት

- በዚህ 6 ወር የፋይቶ ሳኒታሪ ሰርተፊኬሽን (ePhyto) ከአንድ መስኮት አገልግሎት ጋር /ESW/ Integrate የማድረግ ስራ፣ቫሊዴት እንዲሁም ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር የመግባቢያ ሰነድ ላይ የመፈራረም ስራዎች ተሰቷል።
- በዚህ 6 ወር የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬትን ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ እንዲሆን የክትትል ስራ ተሰቷል።
- በዚህ 6 ወር በሰራ ክፍሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለመረጃነት እንዲያገለግሉ ወደ መረጃ ቋት እንዲገቡ እንዲሁም ብሔራዊ የመረጃ ቋት ስርዓት ለመዘርጋት Twining Fiche program እንዲተገበር ክትትል ተደርጓል።

### 2.2.4 ሌሎች ተጨማሪ የተሰሩ ስራዎች

**በፀረ ተባይና ማዳበሪያ ሪጉላቶሪ ሥራ አስፈጻሚ ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት**

- ከፀረ-ተባይ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ያሉ ስጋቶችን አስመልክቶ ጥናት(assesment) በአዲስ አበባ ከተማ ተመረጡ አከባቢዎች(ቦሌ፤ለሚ ኩራ፤አቃቂ ቃሊቲና ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተሞች) ላይ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተደዳር አርሶ አደር ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመሆን ተሰርቷል። ጥናቱም በቀጣይ ያሉ ስጋቶችን ናሙና በመውሰድ በቤተ-ሙከራ የስጋት ደረጃውን ለመለየት የሚሰራ ይሆናል።

- የፀረ-ተባይ አስመጪ  ተቋማት ላይ የፀረ-ተባይ አየያዝ እና ተያያዥ ሕጋዊ ሰነዶች ላይ ኢንስፔክሽን ሥራ ተሰርተው ያሉ ክፍተቶችና ጠንካራ ጎኖች ላይ ምክረ አሳብ ቀርቧል፡፡

- በምስራቅ ሸዋ አከባቢ ባሉየግል እርሻዎች እና መደብሮች በመገኘት የፀረ-ተባይና ማዳበርያ አያያዝ እና አጠቃቀም እንዲሁም ከፀረ-ተባይና ማዳበርያ ቁጥጥር ጋር በተያያዘ በአካባቢው ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመፈተሽ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ የማቅረብ ተግባር ተከናውኗል፡፡

- በግብርና ሚኒስቴር ማሻሻያ የተጠየቀባቸው አራት የማዳበሪያደረጃዎችንማለትም CES 59:4 UREA ,CES 68:28 DAP ,ES 406:2006 ,ES 407;2006  የማዳበሪያ ደረጃ ኮሚቴ 15 አባላት በጋራ በመሆን የማሻሻል ስራ ተሰርቷል፡፡

- ደረጃ ያልወጣላቸ የባዮስቲሙላንትና የናኖ ማዳበሪያዎች የምዝገባ ጋይድላይን ዜሮ ድርፍት የማዘጋጀት ስራ የተከናወነ ሲሆን ለባለድርሻ ለማስተቸት ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

**በእፀዋት ኳራንቲን መሪ ሥራ አስፈጻሚ**

- በዚህ ሩብ ዓመት High-Level Regional SPS Conference በማካሄድ፡
- በተsሙ እና በስራ ክፍሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የማስተዋወቅ ሥራ እንደተሰራ፣
- ተsሙን እና የሥራ ክፍሉን ሲደግፉ የነበሩት መንግስታዊ፣መንግስታዊ ያልሆኑ ተsማት፣ ኢንባሲዎች እና የግል ባሀብቶች እውቅና የተሰጠበት መድረክ፣
- አብሮ የመስራት፣ የመተባበር፣ የመቀናጀት እና የተለያዩ ልምዶችን የተቀሰሙበት መድረክ እንደሆነ፣
- በአህጉራዊ እና በዓለማቀፋዊ ደረጃ ትብብርን ለማሳደግ እና አቅምን ለማጎልበት ዋና ቁልፍ መድረክ እንደሆነ፣ ታይቷል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት የስራ ክፍሉን የአገልግሎትና የአገልግሎት ስነ-ምድብ / Service Taxonomy፣ የአገልግሎት ስታንዳርድ / Service Standard፣ የአገልግሎት ፍሰትና ማፒንግ / Workflow and Service Process Mapping እና የአገልግሎት ካታሎግ / Service Catalogue ተሰርተዋል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት በስራ ክፍሉ በPCE TOOL የተዩ ክፍተቶች መሰረት ያደረገው የ 5 ዓመት እስትራትጂክ እቅድ ጸድቆ የመጨረሻው ሰነድ ህትመት ላይ ነው፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት የTwining Fiche Work plan ተዘጋጅቷል፡፡

- በዚህ ሩብ ዓመት የስራ ክፍሉ እና የጣቢያ ባለሙዎች COLEAD ሥልጠና እንዲያገኙ Action plan ተዘጋጅቶ ተልኳል፡፡
- በዚህ 6 ወር የስራ ክፍሉን ስራዎች ሊያግዝ የሚችል GIZ የበጀት ድጋፍ እንዲያደርግ ፕሮጀክት Concept note ተዘጋጅቶ እንዲፈቀድ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡
- በዚህ 6 ወር በመንገደኛ ለሚገቡና ለሚወጡ የዕፅዋት ምርት ላይ ፍተሻ እንዲካሄድ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ላይ ክትትል ተደርጎል፡፡
- በዚህ 6 ወር Soyameal ወደ ቻይና ለመላክ መግባቢያ ሰነድ /Protocole/ ተፈርሞ የምዝገባ ተጀምሯል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት የCassava ምርት ወደ ቻይና ለመላክ የመጨረሻ አስተያየት የተደረገበት መግባቢያ ሰነድ/Protocole/ ለፊርማ ተልኳል፡፡

**በእፀዋት ላብራቶሪ ሌሎች የተከናወኑ ስራዎች**

- የስራ ክፍሉን ስራዎች ለመደገፍ እና በተሻለ ደረጃ ለማጠናከር የሚያስችል ተጨማሪ የበጀት (የፋይናንስ) ምንጮችን ለማፈላለግ ይቻል ዘንድ የተለያዩ የበጀት ማፈላለጊያ ሰነዶች ተዘጋጅተው በጀት የማፈላለግ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከዚህ ቀደም ከስራ ክፍሉ ጋር በጋራ እየሰሩ ከሚገኙ ድርጅቶች በተጨማሪ በ2018 ዓ.ም በመጀመሪያው 6 ወር ከአንድ አጋዥ ድርጅት ጋር (ማለትም ከፒቲቢ (PTB)) ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል ግንኙነት ለመፍጠር ተችሏል፡፡
- ለምግብ ጥራት እና ደህንነት ምርመራ ላቦራቶሪ ስራ አስፈላጊ የሆኑ በበጀት አመቱ ለማከናወን ከታቀዱ የቅድመ የጥራት አስተዳደር ስርአት ትግበራ ሰነዶች ውስጥ ስምንት (8) ረቂቅ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፡፡
- የእጽዋት ዘር ፍተሻ ላቦራቶሪ የISTA የሶስተኛ ወገን አለም አቀፍ እውቅና (አክሪዲቴሽን) መስፈርቶችን ለማሟላት አስፈላጊ የሆኑ ሰማንያ ሁለት (80) የጥራት ትግበራ ስርዓት ሰነዶች እና ፎርማቶች በማዘጋጀት በባለስልጣን መስሪያ ቤታችን የበላይ አመራሮች/ሀላፊዎች አስገምግሞ አጸድቋል፡፡
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በአሁን ሰአት የተዘጋጁትን ሰማንያ ሁለት (80) የጥራት ትግበራ ስርዓት ሰነዶች እና ፎርማቶች ለግምገማና አስተያየት ለማህበሩ (በISTA) የላከ ከመሆኑም በተጨማሪ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የመጨረሻ ምእራፍ የሆነውን የሲስተምና ቴክኒካል ኦዲት በላቦራቶሪያችን ላይ እንዲያካሄት ለማህበሩ ጥያቄ አቅርቦ

የማህበሩን ምላሽ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ላቦራቶሪ በአሁን ሰአት በመጨረሻው የእውቅና ምእራፍ ላይ ይገኛል፡፡

- ከኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በእጽዋት ዘር ጥራት ፍተሻ ላብራቶሪ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ የፍተሻ/የምርመራ መሳሪያዎችና ሌሎቾ ተያያዥ ቁሳቁሶች ላይ የትክክለኛነት ምዘና (ካሊብሬሽን (Calibration)) እና የማረጋገጫ ስራ በኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት አማካኝነት ተሰርቷል፡፡ በተያያዘም በኢንስቲትዩት ለመሳሪያዎቹ የትክክለኛነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ተሰጥቷል፡፡
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ጉርድ ሾላ አካባቢ ባገኘው አዲስ ቦታ ላይ በአሁን ሰአት በእጽዋት ዘርፉ የምግብ ጥራትና ደህንነት ምርመራ/ፉተሻ አገልግሎት የሚሰጡ ሁለት (ማለትም፡ የኬሚካል ቅሪት ምርመራ ላቦራቶሪ እና የማይኮቶክሲን ምርመራ ላቦራቶሪ) ላቦራቶሪዎችን የማቋቋም ስራ በዚሁ በመጀመሪያው 6 ወር እቅድ ውስጥ ለማጠናቀቅ ተችሏል፡፡
- በ2018 ዓ.ም በሁለተኛው ሩብ ዓመት የእፅዋት ግብዓትና ምርት ምርመራ ላብራቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ጉርድ ሾላ በሚገኘው ቦታ ሌላ አዲስ ሶስተኛ ላቦራቶሪ (የእፅዋት ጤና (የእፅዋት ኳራንታይን ተባይ ዲያግኖሲስ ላቦራቶሪ)) የማቋቋም ስራ ጀምሯል፡፡
- ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ የእፅዋት ላቦራቶሪ የምርመራ መሳሪያዎች፣ የላቦራቶሪ ሶልቨንቶች፣ ሪኤጀንቶች፣ ኪቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእፅዋት ላቦራቶሪ ቁሳቁሶች የሚገቡባቸውን መስፈርቶች መሟላታቸው ተረጋግጦ ለ2 ድርጅቶች የጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ ተሰጥቷል፡፡

**በዝርያ ዘር ቁጥጥር ሪጉላቶሪ ሌሎች የተከናወኑ ስራዎች**

- ከዚህ ቀደም በግብርና ሚንስቴር እና አግራ ፕሮጀክት አማካኝነት ተጀምሮ የነበረን የዘር ዲጂታላይዜሽን ስራ ለማስቀጠል ከሌላኛው የዘረ ሲሰተም seed hub ጋር የሚቀናጅበት/የሚመጋገበበት ሁኔታን እና በሁለቱም ሲስተሞች ዙሪያ ያሉ ክፍተቶችን ለመለየት ከግብርና ሚንስቴር የኤሲቲ ኃላፊውን ጨምሮ 3 ተሳታፊዎች፤ የሚንስትሩ በዘር ዙሪያ አማካሪ፣ ከግብዓት ዘርፍ ኃላፊውን ጨምሮ 2 ተሳታፊዎች፣ ስራውን ከሚደግፉ ፕሮጀክቶች 4 ተሳታፊዎች፣ ሶፍት ዌሮቹን ካበለጸጉ ድርጅቶች 4 ባለሙያዎች፣ ከባለስልጣን መስሪያቤታችን 3 ባለሙያዎች ሆነን በጋራ ገምግመን የድርጊት መርዓ ግብር በማውጣት ስራውን ለማገባደድ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

- በሂደት ላይ የነበሩ 16 የአትክልት ችግኝ የደረጃ ዝግጅቶች ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር በመሆን መሬት ላይ ያለውን ተጨባጭ ሁታ ለመረዳት የመስክ ጉብኝት በማድረግ የእርማት ስራ ተሰርቷል ደረጃዎችን ለማጸደቅ ክትትል እተደረገ ይገኛል፡፡
- የዘር አዋጅ 1288/2015 መጽደቅን ተከትሎ የትግበራ ልምምድ ምዕራፍ (Piolting) በተመረጡ ሰብሎች ዝርያ አለቃቅና አመዘጋገብ ስርዓት በስንዴና ገብስ ሰብሎች የዝርያዎች ባህሪ መገለጫ / Distincitness, Uniformity and Stability / DUS ፍተሻ በሆለታ፣ ቁልምሳ እና በቢሾፍቱ የምርምር ማዕከላት የዝርያ ብቃት / National performance Trial / NPT በሌሎች በተመረጡ የክልልና የፌደራል ምርምር ማዕከላት የተከናወነ ሲሆን ለመታየት የሚቻልባቸው ቦታዎች ላይ ግምገማው እየተከናወነ

- የዝርያ ብቃትና ባህሪ ፍተሻ ቦታዎችን ለማግኘት ጥረት ተደርጎ ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በሶስት ማዕከላት፣ ቢሾፍቱ፣ ቁሉምሳ እና ሆለታ በጊዛዊነት መሬት መጠቀም እንድንችል የተፈቀደ ሲሆን የሶስትዮሽ የመግባቢያ ሰነድ መፈራረም ተችሏል፡፡
- በግብርና ሚነስቴር አማካኝነት በተቋቋመው የዘር ቴክኒካል ኮሚቴ አማካኝነት በሚደረገው ሀገራዊ የዘር መድረክ ላይ ተቋማችንን በመወከል ተሳትፎ ተደርጓል፡፡
- የዘር ላብራቶሪ የአክርዲቴሽን የዶክመንት ዝግጅት ስራ ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፣

# 3. የእንሰሳት ምርትና ግብዓት ቁጥጥር ዘርፍ

## 3.1 የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

- ባለፉት ስድስት ወራት 12500 ቶን ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ደህንነቱና ጥራቱን ጠብቆ ለወጭ ገበያ ኣእንዲቀርብ ለማስቻል፣ ለሰው ምግብነት ለሚውል የስጋ ምርት የኢንስፔክሽን አገልግሎት በመስጠት ፣የቅድመና ድህረ እርድ ምርመራ በማከናወን እና የቄራዎችን ሀይጅንና ሳኒቴሽን የተጠበቀ እንዲሆን በመቆጣጠርና በላቦራቶሪ ምርመራ ጭምር የስጋ ደህንነት እንዲረጋገጥ በማድረግ ለኤክስፖርት ብቁ የሆነ፣ ጤንነቱ ደህንነቱንና ጥራቱን የተጠበቀ ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ለማስቻል ታቅዶ በድምሩ በ11375 ቶን

ስጋ እና ተረፈ ስጋ ላይ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 91 % ሊሆን ችሏል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 3.1.1 የቅድመ ዕርድ ምርመራ የተደረገላቸው የቁም እንስሳት

- በ6 ወሩ 1350 ሺ.ህ እንሰሳት የቅድመ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ በድምሩ 1215 ሺ.ህ ተከናውኗል፡፡ ይሄም የእቅዱ 90 % ነው፡፡
- በአጠቃላይ 13.5 ሺ.ህ (1%) እንሰሳት በቅድመ እርድ ምርመራ ውድቅ የተደረጉ ቢሆንም ይህም ከጊዜ ወደ ጊዜ በተደረገው የኢንስፔክሽን ስራ እየቀነሰ ቢመጣም ወድቅ ለተደረጉት እንሰሳት ዋነኛ ምክንያታቸው
  - የእንሰሳት ክብደት ትልቅ መሆን እና ከሚፈለገው መጠን ማነስ
  - ሲጓጓዙ የእንሰሳት የሰውነት መጉዳት፣
  - የበሽታ ምልክት መታየት፤

### 3.1.2 የድህረ ዕርድ ምርመራ የተደረገላቸው የታረዱ እንስሳት

- በ6 ወሩ 1345 ሺ.ህ እንሰሳት የድህረ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 1197 ሺ.ህ ተከናውኗል፡፡ ይህም የእቅዱ 89% ነው፡፡
- በድህረ እርድ ምርመራ ከተመረመሩት ውስጥ 27 ሺ.ህ (2%) ውድቅ ተደርጓል፡

✓ ከዚህ ጋር ተያይዞም **ባለፉት 6 ወራት ደህንነቱና ጥራቱ ተረጋግጦ ወደ ተቀባይ አገራት ለሚላክ ስጋና ተረፈ ስጋ** ምርቶች 4500 የደህንነትና ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ4050 (90 %) ለማከናወን ተችሏል፡፡

✓ ባለፉት ስድስት ወራት ለ16 የስጋና ተረፈ ስጋ አምራች ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ16 የስጋና ተረፈ ስጋ አምራች ተቋማት ኤክስፖርት ቄራዎችን/ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ እድሳት አገልገሎት ተሰጥቷል፡፡

### 3.1.3 የእንስሳት ምርት ጥራትና ደህንነት በላቦራቶሪ ምርመራ ማረጋገጥ

✓ እስከዚህ ሩብ አመት በ 365 የእንስሳት ተወጽኦ ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ በ 393 (>100%) ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ፍተሻ ሥራ ማከናወን ተችሏል፡፡ የ 2ኛ ሩብ አመት ዝርዝር አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

✓ የጥሬ ወተት የምግብ ንጥረ ነገር ይዘት ምርመራ ከተሰራላቸው 85 ናሙናዎች ውስጥ 65.9% (56/85) የቅባት (ፋት) መጠን ከደረጃ በታች ሲሆን 9.4% (8/85) የጥሬ ወተት ናሙናዎች ፍሪዚንግ ፖይንት ደግሞ ተፈለጊውን ደረጃ ሳያሟላ ቀርቷል፡፡

- ✓ የጥሬ ወተት አፍላቶክሲን የላቦራቶሪ ምርመራ ከተሰራለቸው 85 ናሙናዎች ውስጥ በ 5.9% (5/85) ላይ የአፍላቶክሲን ብክለት መጠን ከሚፈለገው ደረጃ በላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ የማይክሮባዮሎጂ ጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ከተሰራላቸው 144 የእንስሳት ምርት ወይም ተዋጽኦ ናሙናዎች ውስጥ በ 42.4% (61/144) በሽታ አምጪ ባክቴሪያዎች የተለዩ ሲሆን እነሱም ኢኮላይ (63.9%)፣ ስታፍሎኮከስ አውረስ 34.4%) እና ሳልሞኔላ (1.6%) ናቸው፡፡
- ✓ በአጠቃላይ ባለፉት 6 ወራት በ189 የጥሬ ወተት ናሙናዎች ላይ የአፍላቶክሲን እና የምግብ ንጥረ ነገር ይዘት የፊዚኮ-ኬሚካል ምርመራ እንዲሁም በ 204 የእንስሳት ምርት (159 ሥጋ፣ 33 ወተት እና 12 እንቁላል) ናሙናዎች ላይ ደግሞ የማይክሮባዮሎጂ ጥራትና ደህንነት ምርመራ በእቅድ ከተያዘው በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡
- ✓ የጸረ ተዋስያን መድኃኒት በጀርሞች መላመድ ምርመራ አገልግሎት በተመለከተ፡- እስከዚ 2ኛው ሩብ ዓመት ከእንስሳት ምርትና መኖ ናሙናዎች ላይ በማይክሮባዮሎጂ ምርመራ በተለዩ 61 ባክቴሪያ (ኢኮላይ እና ስታፍሎኮከስ አውረስ) ላይ ከ 8 በላይ የተለያዩ መድኃኒቶችን በመጠቀም የጸረ ተዋስያን መድኃኒት በጀርሞች መላመድ ምርመራ ማካሄድ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት ኢኮላይ ለአምፕሲልን (100%) ለስትርብቶማይሲን (56.4%) እንዲሁም ስታፊሎኮከስ አውረስ ለፔኔሲልን (100%) እና ለቴትራሳይክልን (66.7%) ከፍተኛ የሆነ የጸረ ተዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መላመድ ችግር አሳይቷል፡፡

ምክረ-ሐሳብ፡- በጥሬ ወተት ምርት ናሙናዎች ላይ የተገኘው ከፍተኛ የጥራት ችግር (ያልተፈለገ ቅየጣ) እና የወተት አፍላቶክሲን እንዲሁም በእንስሳት ምርት ወይም ተዋጽኦ ናሙናዎች ምርመራ ላይ የታየው የጎጂ ተዋስያን ብክለት እና የጸረ ተዋስያን መድኃኒት በጀርሞች መላመድ ችግር አገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የጤና ስጋት በመሆናቸው በንጽህና አያያዝ እና በእንስሳት መድኃኒት አጠቃቀም እና ቁጥጥር ላይ በትኩረትና በስፋት ሊሰራ ይገባል፡፡

- ✓ ባለፉት 6 ወራት በ46 የኮመርሻል የእንስሳት ውጤት ጥሬና በከፊል የተዘጋጀ ምርት አምራች ድርጅቶች ላይ የኦዲት ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ (100%) ተከናውኗል፡፡ በዚህ መሰረት
- በኮሜርሻል ዶሮ እርባታ ላይ የተሰማረቱን አምራቾች መልካም የአመራረት ሥርዓት (GMP,GHP) አተገባበር ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በድጋፍና ክትትል በመለየት የማስተካከያ እርምት አካሄደው ወደ ምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማውጣት ሂደት እንዲገቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ተሰርቷል፡፡

- የክልል ተሻጋሪ የስጋ ምርት የሚያካሄዱ 5 የሀገር ውስጥ ቄራዎችና አዲስ አባባ ውስጥ የሚገኙ 3 ቄራዎች የመስክ ጉብኝት በማካሄድ የምርት ጥራት፣ጤንነትና ደህንነት ያሉበትን ደረጃ የመለየት እና በሂደት ወደ ምዝገባ ስርአት የሚገቡበትን ሁኔታ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የጋራ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

✓ ባለፉት ስድስት ወራት በ30 የእንስሳት ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ በ30 ተቋማት ላይ (100%) ልማክናወን ተችሏል፡፡

**በቅንጅት የተፈፀሙ ተግባራት**

- የስጋ እና የተረፈ ስጋ ኤክስፖረቱን ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ማለትም ከኤርፖርት ካርጎ፣ ከጉምሩክ ኮሚሽን፣ ከብሔራዊ ደህንነት፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከብሔራዊ ባንክ፣ ከግብርና ሚኒሰቴር፣ ከንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒሰቴር፣ከወተት እምራቶች፣ ከዶሮ አረቢ ማህበር፣ ከስጋ አምራች እና ላኪዎች ማህበር፣ ከሁሉም ኤክስፖርት ቄራዎች እና ከቀራ ስርቢስ ተጠቃሚዎች ከድራይብ ፕሮጅቸት ባገኘነው የገንዘብ ድጋፍ ከሬጉላቶሪ አኳያ ባሉ መልካም አጋጣሚዎች እና ተግዳሮቶች ዙሪያ ውይይት ተርግጓል፡ ፡
- ከጆርዳን መንግስት ጋር በተደረገ ተደጋጋሚ ውይይት እና የጆርዳን ሬጉላቶሪ ተቋማት ሀላፊዎች መጥተው የኢትዮጲያ ስጋ ወደ ጆርዳን መላክ ተጀምሯል፡፡
- የስጋ ምርት ለመላክ የሚያስችል የሁለቱሽ ስምምነት ለሌላቸው አልጀሪያ፣ሞሮኮ እና ቱኒዚያ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ግንኙነት ተፈጥሮ ስምምነት ላይ እንዲደረስ ለኢትዮጲያ ስጋ አምራች ቄራዎች የድጋፍ ደብዳቤ ተጽፎሏቷል፡፡
- በኤክስፖርት ቄራዎች ላይ የሚታዩትን የቆሻሻ አያያዝና አስተዳደርር ችግሮች ለማስተካከል እንዲቻል በጊዜ ገደብ የተቀመጠ የማስተካከያ እርምት እንዲያካሄዱ በደብዳቤ የማሳወቅ እና በተቀመጠው ሰሌዳ ባያስተካክሉ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚወሰድ በመግለፅ በአጭር ጊዜ ወደ ተግባራዊ ስራ እንዲገቡ ለማስቻል ጥረት ተደርጓል፡፡
    - የተቀመጠውን የጊዜ ገደብ ባለማከበሩ የአቢሲኒያ ኤ/ቄራ ላይ እርምጃ ተወሰዳል፡፡
    - የስጋ ሴክተሩን ዲጅታላዝ ለማድረግ ሲሰተሙ አልቆ ለባለሞያዎች ስልጠና ተሰጥቶ ወደ (በሰርቢስ ዲጅታላይዜሽን፣ኢ-ለርኒግ እና ዌብሳይት) ተግባር እንዲገባ ተደርጓል፡፡

- የኦዲት ኢንስፔክሽን ግኝት መሰረት በማድረግ የዶሮ ቁራ አቋቁመው በመስራት ላይ የሚገኙ አምራቾች በመስክ ደጋፍና ክትትል ችግሮችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲያካሄዱ  ውይይት በማካሄድ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡
- በድምር 11 የዶሮ ወላጅ  አስመጭና  አከፋፋይ  ድርጅቶች፣እንቁላል  ጣይ እርባታዎች፣የስጋ ዶሮ እርባታዎች እና የዶሮ ቁራ በአመራረት ሂደት ላይ ኦዲት ኢንስፔክሽን ስራ  በመስራት የብቃት ማረጋገጫ ሰርፊኬት ተሰጥቷል ፡፡
- በ2 የዶሮ ቁራዎች እና በ2 የዶሮ ፋርም ላይ በኦዲት ግኝት መሰረት ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ጉድለታቸውን እንዲያስተካከሉ ተደርጓል፡፡
- ከSNV Bridge+ ፕሮጀክት ጋር በመተባባር በ71 የወተት አምራች  የኦዲት ኢንስፔክሽን ተከትሎ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- የእንስሳት ምርትና ማምረቻ ተቋማት ምዝገባ ለማካሄድና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የፈቃድ እና ምዝገባ መመሪያ draft ተዘጋጅቷል፡፡
- ከSNV Bridge+ ፕሮጀክት ጋር በመተባበር የወተት ምርት መልካም የአመራረት አተገባበር (GMP,GHP) እና ንጽህና አጠባበቅ ላይ ለባለሙያዎችና ባለድርሳ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- 
- ሌሎች የእንሰሳት ምርቶችን (ወተት፣ ማር፣ እንቁላል፣ዓሣ) ለሚያቀናብሩና ለሚያደራጁ ድርጅቶች ከክልሎች ጋር በመሆን  20 ድርጀቶች ተመዝግቧል፡፡
- የእንሰሳት ምርት ጥራት፣ጤንነትና ደህንነት  የሬጉላቶሪ  ስራዎችን  የሚያግዙ መመሪያዎች በሁሉም የምርት አይነቶች የመጀመሪያ ድራፍት ማዘጋጀት ሂደት ወደ ማጠናቀቅ ይገኛል፤
- ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ከእንስሳት ምርት ጥራት፣ ጤንነት እና ደህንነት ጋር የተያያዙ 4 ነባር ስታንዳርዶች የመከለስ ስራ ተሰርቷል፡

## 3.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች

- ✓ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት 316,000 የቁም እንስሳትን (ዳልጋ ከብት፣ ግመል፣ በግና ፍየል) በኳራንቲን ጣቢያዎች በማቆየት የጤና ምርመራና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ፣ ለ 306,085 እንስሳት የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ወደ ውጭ ሀገር እንዲላኩ ተደርጓል:: ይህም የዕቅዱን 97% ስኬት ያሳያል::
- ✓ በስድስት ወሩ ውስጥ ጥራቱ፣ ደህንነቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የሚላክ 282,000 የአንድ ቀን ጫጩት እና የለማ እንቁላል ኤክስፖርት ለማድረግ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ ምንም ዓይነት ክንውን አልተመዘገበም (0% አፈጻጸም):: በ 6 ወሩ ይከናወናል ተብሎ የታቀደው ኤክስፖርት መጠን ያልተከናወነበት ምክንያት የገበያ ፍላጎት በማጣቱ ሳይሆን፣ በሀገር ውስጥ የሚታየውን ከፍተኛ ፍላጎት ለማሟላትና የሀገር ውስጥ ገበያን ለማረጋጋት ሲባል በግብርና ሚኒስቴር እና በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ውሳኔ ወደ ውጭ የመላክ እቀባ በመጣሉ ነው::
- ✓ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ 103 ቶን ሰምና ማር ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ፣ ለ 79.063 ቶን ምርት የሳኒተሪ ሰርተፍኬት በመስጠት ወደ ውጭ ሀገር እንዲላክ ተደርጓል:: ይህም ከእቅዱ አንጻር 76.8% አፈጻጸም መመዝገቡን ያሳያል::
- ✓ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት 2,200,000 ያለቀለት ቆዳና ሌጦ ላይ የቁጥጥርና የኢንስፔክሽን ሥራ በማከናወን የሳኒተሪ ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ፣ ለ 2,001,840 ምርቶች አገልግሎቱ ተሰጥቷል:: ይህም ከዕቅዱ አንጻር 91% አፈጻጸም መመዝገቡን ያሳያል::
- ✓ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ጤንነቱና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የሚገባ 369,246 የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል ለማስገባት ታቅዶ፣ ለ 1,775,681 ምርቶች የኢንስፔክሽንና የቁጥጥር ስራ በማከናወን ወደ ሀገር እንዲገቡ ተደርጓል:: ይህም ከዕቅዱ አንጻር >100% የሆነ እጅግ የላቀ አፈጻጸም ነው:: ለዚህ አፈጻጸም ከፍተኛ መሆን ዋነኛው ምክንያት "የለማት ትሩፋት" አገራዊ መርሃ-ግብር በዘርፉ ላይ የፈጠረው ከፍተኛ መነቃቃትና በሀገር ውስጥ የታየው ሰፊ የዶሮ እርባታ ፍላጎት ነው:: መንግስት ለዘርፉ የሰጠው ልዩ ትኩረትና የተቀናጀ የሥራ ዕድል ፈጠራ ተግባራት ለግብዓቶቹ ፍላጎት መጨመር አስተዋጽኦ ያደረጉ ሲሆን፣ ተቋሙም የሬጉላቶሪና የቁጥጥር አገልግሎቱን በማቀላጠፍ የምርቶቹን ጤንነትና ጥራት በማረጋገጥ ወደ ሀገር እንዲገቡ አድርጓል::
- ✓ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ጤንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ 165 የተሻሻለ ዝርያ ያለው ዳልጋ ከብት ለማስገባት ታቅዶ፣ በክንውን 535 ከብቶችን ማስገባት ተችሏል:: ይህም ከዕቅዱ አንጻር >100% የሆነ እጅግ የላቀ አፈጻጸም መመዝገቡን ያሳያል:: ይህ ከፍተኛ ስኬት በሀገር ውስጥ ያለውን የወተት ምርታማነት ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ሲሆን፣ ተቋሙም አስፈላጊውን የጤና ምርመራና የኳራንቲን ቁጥጥር በማድረግ ምርጥ ዝርያ ያላቸው ከብቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ አመቻችቷል::

- ✓ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ 80,000 የእንስሳት አባላዘር (Semen) ለማስገባት ታቅዶ፣ 73,450 አባላዘር ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል። ይህም ከዕቅዱ አንጻር 91% አፈጻጸም መመዝገቡን ያሳያል። ተግባሩ የተከናወነው ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ መስፈርቶችን ባከበረ መልኩ ሲሆን፣ ከመግባታቸው በፊት ጥብቅ የእንስሳት በሽታ ስጋት ዳሰሳ (Risk Assessment) በማድረግ የሀገር ውስጥ ዝርያዎችን ደህንነት ባረጋገጠ መልኩ ተፈጽሟል።
- ✓ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ለቁም እንስሳት፣ ለእንስሳት ምርቶች እና ለተረፈ ምርቶች ኤክስፖርት ዘርፍ በተሰማሩ 33 ድርጅቶች ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን ታቅዶ፣ በ 37 ተቋማት ላይ የቁጥጥር ሥራው ተፈጽሟል። ይህም ከዕቅዱ አንጻር >100% አፈጻጸም ያስመዘገበ ሲሆን፣ በተቋማቱ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት የጥራትና የሬጉላቶሪ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የውጭ ንግድ ሂደቱ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን አስችሏል።
- ✓ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ከውጭ ለሚገቡ የእንስሳት ግብዓቶች (የአንድ ቀን ጫጩት፣ የዘር ፈሳሽ፣ የለማ እንቁላልና ጊደሮች) የጤናና የጥራት ደረጃን ለማረጋገጥ 1,700 ናሙናዎችን ለማስመርመር ታቅዶ፣ በክንውን 1,598 ናሙናዎች እንዲመረመሩ ተደርጓል። ይህም ከዕቅዱ አንጻር 94% አፈጻጸም መመዝገቡን ያሳያል። ስራው ከእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ጋር በቅንጅት የተከናወነ ሲሆን፣ ይህም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ግብዓቶች ከማንኛውም በሽታ ነፃ መሆናቸውንና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ታስቦ የተከናወነ ቁልፍ የጥራት ቁጥጥር ተግባር ነው።
- ✓ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት በተቀባይ ሀገራት መስፈርት መሠረት ለኤክስፖርት ለተዘጋጁ 80,000 የቁም እንስሳት የደም ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ፣ ለ 103,123 እንስሳት ምርመራው ተከናውኗል። ይህም የዕቅዱን >100% በማሳካት የላቀ አፈጻጸም የታየበት ተግባር ነው። በምርመራው ውጤት መሠረት የጤና ችግር የተገኘባቸው 11,240 እንስሳት ወደ ውጭ እንዳይላኩ ተለይተው የተቀነሱ ሲሆን፣ ይህም በተቀባይ ሀገራት ላይ ሊከሰት ይችል የነበረውን የጤና ስጋትና በሀገሪቱ የውጭ ንግድ ላይ ሊፈጠር ይችል የነበረውን እገዳና መስተጓጎል አስቀድሞ ለመከላከል አስችሏል።

## 3.3 ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት

- ✓ **ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት**

በ2018 በጀት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት 1750 ቶን ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ወይም ተመርቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ታቅዶ 2195.09 ቶን የእንስሳት መድኃኒት ጥራቱ፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ እንዲረጋግጥ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም >100% ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ተገልጋዮች አገልግሎቱን ፈልገው በብዛት ባመምጣታቸው ነው፡፡

✓ **ተገምግሞ፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ የተመዘገበ የእንስሳት መድሃኒት**

በ2018 በጀት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት 60 የሚሆኑ የእንስሳት መድሃኒቶችን በመገምገም፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ በማረጋግጥ ለመመዝገብ ታቅዶ 80 የእንስሳት መድኃኒት እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም >100% ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት አሰራሩ ዲጂታላይዝድ ከሆነ በኃላ አምራች ድርጅቶች ከሀገር ውስጥ ባለ ተወካይ በተጨማሪ የምዝገባ ሂደቱን የሚከታተሉት በመሆኑና የተለያዩ የመድሃኒት አማራጮች የመመዝገብ እድል በመፈጠሩ ነው፡፡

**የመድሃኒት ናሙዎችን ላይ የተካሄደ የጥራት፣ ደህንነት እና ፈዋሽነት የላቦራቶሪ ምርመራ**

✓ **የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት**

በ2018 በጀት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት ለ350 የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመሰጠት ታቅዶ ለ321 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰቷል፡፡ አፈጻጸሙም 91.5% ሆኗል፡፡

- **ለነባር የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ የሙያ ፈቃድ ማደስ**

  በ2018 በጀት ዓመት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት 522 ለነባር የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ለማደስ ታቅዶ ለ 474 (90.08%) ባለሙያዎች ማደስ ተችሏል፡፡

- **ለአዲስ የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ የሙያ ፈቃድ መስጠት**

በ2018 በጀት ዓመት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት ለ 50 አዲስ የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ የሙያ ፈቃድ አገልግሎት እንሰጣለን ብለን አቅደን ለ 61 የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያዎች አዲስ የሙያ ፍቃድ ሰጥተናል ንጽጽሩም 122% ሆኗል። አፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ተገልጋዮች አገልግሎቱን ፈልገው በብዛት በመምጣታቸው ነው።

- **የባለሙያ ለውጥ ፈቃድ መስጠት**

በ2018 በጀት ዓመት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት ለ 40 ድርጅቶች የባለሙያ ለውጥ ፈቃድ አገልግሎት እንሰጣለን ብለን አቅደን 28 ድርጅቶች የባለሙያ ለውጥ ፈቃድ ተደርጓል። አፈጻጸሙም >70% ሆኗል። አፈጻጸሙም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ተገልጋዮች አገልግሎቱን ፈልገው በብዛት ባለመምጣታቸው ነው።

- **የመጋዘን ለውጥ ፈቃድ መስጠት**

በ2018 በጀት ዓመት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት ለ13 ድርጅት የመጋዘን ለውጥ ፍቃድ እና የተጨማሪ መጋዘን ፈቃድ እንሰጣለን ብለን አቅደን ለ16 ድርጅት የመጋዘን ለውጥ ፈቃድ ተደርጓል አፈጻጸሙም 123% ሆኗል።

**የእንስሳት መድኃኒቶች እና የህክምና መገልገያ ለማስተዋወቅ የሚቀርቡ ጥቄዎችን ማስተናገድ**

በ2018 በጀት ዓመት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት 1 የእንስሳት መድኃኒቶች እና የህክምና መገልገያ ለማስተዋወቅ የሚቀርቡ ጥያቄ እናስተናግዳለን ብለን አቅደን 5 (>100%) ተከናውኗል።

✓ **የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን**

በ2018 በጀት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት 341 የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን እናረጋለን ብለን አቅደን 340 የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን አካሂደናል። አፈጻጸሙም 99.7% ሆኗል።

- **የእንስሳት መድሃኒት አስመጪ እና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ላይ ኢንስፔክሽን ማድረግ**

እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት በዋና መስሪያ ቤት እና በመዐከላት 341 የእንስሳት መድሃኒት አስመጪ እና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ላይ ኢንስፔክሽን ለማድረግ ታቅዶ 340 የእንስሳት መድሃኒት አስመጪ ድርጅቶች ላይ ኢንስፔክሽን ማካሄድ ተችላል፡፡ አፈጻጸሙም 99.7% ሆኗል፡፡ በኢንስፔክሽን ወቅት ክፍተት የተገኘባቸውን ድርጅቶች ከታች የተዘረዘሩትን ተመጣጣኝ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡

- 3 (1 አስመጪ እና 2 ጅምላ አከፋፋይ) ድርጅቶችን የሶስት ወር እገዳ፣ 9 ድርጅቶች (2 አስመጪ እና 7 ጅምላ አከፋፋይ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ 10 ድርጅቶችን (3 አስመጪ እና 7 ጅምላ አከፋፋይ) የቃል ማስጠንቀቂያ እና 1 በኢንስፔክሽን ወቅት ክፍተት በመኖሩ ተሰርዟል፡፡

ሰንጠረዥ 1፡ የኮንሳይንመንት ናሙና ተወስዶ ከደረጃ በታች በመሆናቸው እንዲወገዱ ወይም ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ የተደረጉ እና በመደረግ ላይ ያሉ መድኃኒቶች በብዛት እና በዋጋ

| SN | Generic Name | Dosage form | Quantity | Unit | Total cost (ETB) | Country of origin |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Oxytetracycline 10 % | Injection | 2150 | Vial | 191,743.20 | India |
| 2 | Oxytetracycline 20 % | Powder | 24756 | sachet | 1,252,653.00 | India |
| 3 | Oxytetracycline 20 % | Powder | 984 | Sachet | 470,155.20 | India |
| 4 | Oxytetracycline 20 % | Powder | 10000 | sachet | 1,234,115.00 | India |
| 5 | Oxytetracycline 20 % | Powder | 189000 | sachet | 2,176,413.53 | India |
| 6 | Oxytetracycline 20 % | Powder | 84800 | Vial | 6,963,002.45 | China |
| 7 | Enroflocaciline | Injection | 744 | Vial | 121,478.44 | India |
| 8 | | Injection | 1383 | Vial | 424,683.24 | India |
| 9 | Tetraclozash | Bolus | 1753 | Box | 1,363,693.76 | India |
| 10 | Ivermectine | Injection | 160000 | Vial | 3,827,439.36 | China |
| 11 | Oxy 10 % | Injection | | Vial | | China |
| 12 | Ivermectine | Injection | 42,500 | Vial | 2,610,241.37 | India |
| | sub total | | | | 15,310,538.63 | |

በመግቢያና መውጫ ኬላ ላይ የጥራት ደረጃቸውን ለማረጋገጥ ለተወሰደ ናሙና ከደረጃ በታች የሆነ

- 10000 boxes Ashoxy 20% Powder እንዲወገድ ተደርጓል፡፡
- 84800 Vial Oxytetracycline 20 % እንዲወገድ ተደርጓል፡፡
- 160000 Vial Ivermectin Injection ወደመጣበት ሀገር እንዲመለስ ተደርጓል፡፡
- 744 vial Enroflocaciline Injection እና 1753 Tetraclozash Box ወደመጣበት ሀገር እንዲመለስ ተደርጓል፡፡
- ሌሎቹ መድሃኒቶች በማስወገድ ወይም ወደመጣበት ሀገር በመመለስ ሂደት ላይ ናቸው፡፡

✓ የእንስሳት መድኃኒት ጥራት ፈዋሽነትና ደህንነት ማረጋገጥ

የመድኃኒት ፊዚኮ-ኬሚካል ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት፡- በዚህ 2ኛ ሩብ ዓመት በ 90 የመድኃኒት ምርት ናሙናዎች ላይ የፊዚኮ-ኬሚካል ጥራትና ደህንነት ምርመራ ለማከናወን ታቅዶ በ 193 ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ፍተሻ ማካሄድ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከመቶ ፐርሰንት በላይ ነው፡፡ እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት (6 ወር) በ 180 ናሙናዎች ላይ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ በ 284 (>100%) ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ ምርመራ ከተሰራላቸው የመድኃኒት ምርት ናሙናዎች ውስጥ 22 (7.7%) የፊዚኮ-ኬሚካል ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ መስፈርት ያላሟሉ ስለሆኑ ተገቢው የሪጉላቶሪ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለመድኃኒት ሪጉላቶሪ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ሪፖርት ተደርጓል፡፡

የመድኃኒት ማይክሮባዮሎጂ ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት፡-በዚህ 2ኛ ሩብ ዓመት በ30 የመድኃኒት ናሙናዎች ላይ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 54 ማከናወን ተችሏል፡፡ እስከ 2ኛው ሩብ ዓመት ድረስ ከታቀደው 60 ናሙና ውስጥ 85 (>100%) መመርመር ተችሏል፡፡ የማይክሮባዮሎጂ ምርመራ ከተሰራላቸው 85 ናሙናዎች መካከል 1 ናሙና (1.2%) የማይክሮብያል ሊሚት ምርመራ መስፈርትን ሳያሟላ በመቅረቱ ተገቢው የሪጉላቶሪ እርምጃ እንዲወሰድበት ሪፖርት ተደርጓል፡፡

የክትባት ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት፡- በዚህ 2ኛ ሩብ ዓመት 5 ታቅዶ 1 የክትባት ምርት ናሙና ወደ አፍርካ ህብረት የክትባት ቁጥጥር ማዕከል በመላክ የጥራትና ደህንነት ምርመራ እንዲሰራለት ተደርጓል፡፡ እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት 10 ታቅዶ በ 6 (60%) የክትባት ምርት ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት ላቦራቶሪ ምርመራ ተሰርቶ ውጤቱ ለመድኃኒት ሬጉላቶሪ ሪፖርት ተደርጓል፡፡ አንድ ክትባት ናሙና በምርመራ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ እስከ አሁን ምርመራ የተደረገላቸው ሁሉም የክትባት ናሙናዎች ተፈላጊውን የጥራትና ደህንነት መስፈርት የሚያሟሉ መሆኑን በላቦራቶሪ ምርመራ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**የእንስሳት መድሃኒት የምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መመሪያዎች ማዘጋጀት ወይም ማሻሻል**

- ✓ በ2018 በጀት 1ኛ ሩብ ዓመት መመሪያ ማለትም የኢንስፔክሽን እና የአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ መመሪያ ድራፍት ለማዘጋጀት ታቅዶ 90% ተዘጋጅቷል፡፡ አፈጻጸሙ 90% ሆኗል፡፡

**በእንስሳት መድሃኒት ሬጉላቶሪ ስር ያሉ አገልግሎቶችን በ ድህረ ገጽ እንዲከናወኑ (ዲጂታላይዝድ) ማድረግ**

- ✓ በ2018 በጀት 1ኛ ሩብ ዓመት 6 በእንስሳት መድሃኒት ሬጉላቶሪ ስር ያሉ አገልግሎቶችን በ ድህረ ገጽ በኢሰርቪስ እየተከናወኑ ሲሆን ወደ 5 የሚደረሱ አገልግሎቶች በ መሶብ ማዕከል እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ሆኗል፡፡

**ስልጠና መስጠት**

- በዋና መስሪያቤት እና በመዓከላት ለሚሰሩ 35 የእንስሳት መድሃኒት ኢንስፔክተሮች በአግባባዊ የእንስሳት መድሃኒት ቁጥጥር እና አጠቃቀም ላይ የሁለት ቀን ስልጠና በ ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

## 3.4 ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ

- ✓ **የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ መኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት**

  በዚህ ስድስት ወራት ለ398 የመኖ **አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ** ንግድ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ326 (82 % ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ተችሏል። በዚህ መሰረት

  - የ144 የመኖ ንግድ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት ለማድረግ ታቅዶ ለ103 የመኖ ንግድ ድርጅቶች እድሳት የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 70 % ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነው ተቋማት ባለመቅረባቸው ሲሆን፣ ዕድሳቱ በቀጣይ ሩብ ዓመታት በቅጣት የሚከናወን ይሆናል፡፡
  - ለ37 አዲስ እና ምትክ የብቃት ማረጋግጫ ለመሰጠት ታቅዶ 20 አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እና 26 ምትክ፣ በድምሩ 46 የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ ›100% ሆኗል፡፡
  - ለ177 የእንስሳት መኖ ባለሙያዎችን የብቃት ማረጋገጫ ዕድሳት ለማከናወን ታቅዶ 118 ሲከናወን፣ አፈጻጸሙ 66.67% ነው፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነው

ዕድሳት ባልተካሄደባቸው የሚሰሩ ባለሙያዎች ባለመቅረባቸው ሲሆን፣ በቀጣይ ሩብ ዓመት በቅጣት የሚከናወን ይሆናል፡፡

- በዚህ ግማሽ ዓመት በመኖ ንግድ ተቋማት ለሚሰሩ 37 አዲስና ምትክ የመኖ ባለሙያዎች ምዝገባና የሙያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፣ 37 አዲስ እና 22 ምትክ በድምሩ 59 የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ ›100% ሆኗል፡፡

✓ በዚህ ግማሽ ዓመት በኦንላይን በኤሌክትሮኒክስ ሲንግል ዊንዶው ለመኖና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪዎች ለ <u>3500</u> ቶን የግዥና የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ 4055 ቶን የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% ሆኗል፡፡

- በዚህ ሩብ ዓመት ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ <u>3000</u> የመኖ ግብዓት በኦንላይን ሲንገል ዊንዶው የመልቀቂያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፣ ከምርቱ ጋር የሚቀርበውን የጥራት ማረጋገጫ ሰነዶችንና በመኖ ኢንስፔክተሮች የፊዚካል ኢንስፔክሽን በማካሄድ **ለ2100** ቶን የመልቀቂያ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን፣ አፈጻጸሙ 70% ነው፡፡ በተሰጠው የግዢና የማስገቢያ ፈቃድ መጠን ስላልቀረበ ነው፡፡

- አዳዲስ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር የሰነድ ግምገማ በማካሄድ በዚህ ግማሽ ዓመት 80 የምርት ዓይነቶችን ለመመዝገብና ወደ አገር እንዲገባ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ በአስመጪዎች የ107 ምርት ጥያቄ ቀርቦ በተደረገው የሰነድ ማጣራት 10 የምርት ዓይነት መስፈርቱን ስላላሟላ ሲወድቅ፣ 80 ምርት ተመዝግቦ ጊዜያዊ የምዝገባ ሰርተፊኬት ተሰጥቷል፣ ቀሪ 17 ምርት በሰነድ ማጣራ ሂደት ላይ ነው፡፡

✓ ለወጪ ንግድ ለሚቀርብ የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ በዚህ ግማሽ 150 የቅድመ ማስወጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት ላሟላ 129 የቅድመ ማስወጫ ሰርተፊኬት የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ 86% ሆኗል፡፡ በዚህ የመኖ ወጪ ንግድ የቅድመ ማስወጫና በጣቢያዎች የመልቀቂያ ፈቃድ ተሰጥቶ <u>25452.5</u> ቶን የመኖ ጥሬ ዕቃ ወደ ተለያየ ሀገራት የተላከ ሲሆን ከዚህ ወጪ ንግድ <u>13,468,816</u> የአሜሪካ ዶላር ለሀገር ማስገኘት ተችሏል፡፡

✓ **ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ የተመረተ የተቀነባበረ መኖ**

በዚህ በግማሽ ዓመት 150,000 ቶን የተቀነባበረ መኖ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለገበያ እንዲቀርብ ታቅዶ 138725 ቶን የተመረተ ሲሆን፣ አፈጻጸሙ 92.48% ሆኗል፡፡

✓ **በእንስሳት መኖ እና ተቋማት ኢንስፔክሽን ማካሄድ፤**

በዚህ ስድስት ወር በ184 የእንስሳት መኖ እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቀዶ 162 ኢንስፔክሽን የተካሄደ ሲሆን አፈጻጸሙም 88.04% ሆኗል፡፡ በዚህ መሰረት

- በ46 የእንስሳት መኖና የመኖ ግብዓት አስመጪ ተቋማት ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ለማካዬድ ታቅዶ 45 (97.83%) እንዲሁም ለቅድም ፈቃድ በ6 ተቋማት በድምሩ 61 ኢንስፔክሽን ተካሂዷል፡፡
- በ4 የመኖ አከፋፋይ ተቋማት ድህረ-ፈቃድ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ ለማዕከላት የተሰጠው ስራ ባለመሰራቱ ምክንያት አልተፈጸመም፡፡ ይሁን እንጂ በቅድመ- ፈቃድ ኢንስፔክሽን በ 1ተቋም ኢንስፔክሽን ተከናውኗል፡፡
- በ20 የእንስሳት መኖ ጥሬ እቃ አምራች ተቋማት ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ 5(25%) የተፈጸመ ሲሆን፣ በ3 ተቋማት ቅድመ-ፈቃድ ኢንስፔክሽን ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነው በመኖ አምራች ተቋማት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ በመሰራቱ ሲሆን፣ በቀጣይ ሩብ ዓመት ስራው ይከናወናል፡፡
- በ62 መኖ አምራች ተቋማት ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ በ65 (>100%) ማከናወን ተችሏል በተጨማሪም በቅድመ ፈቃድ ኢንስክሽን 3 ተከናውኗል፡
- በ52 የመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ላኪ ድርጅቶች ድህረ-ፈቃድ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ በ27 (51.1%) ተቋማት ማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በቅድመ- ፈቃድ ኢንስፔክሽን በ7 ተቋማት ተከናውኗል፡፡
- በ15 የመኖ ግብአት አምራች ድርጅቶችን ወደ ሕጋዊ አሰራር ለማስገባት ታቅዶ 3 የዱቄት ተረፈ-ምርት አምራች ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወስደዋል፣ አፈጻጸሙ 20% ነው፣ ዝቅተኛ የሆነው አገልግሎቱን ፈልገው የሚመጡ ተቋም ባለመኖራው ነው፡፡

- ከመኖ ጥራትና ደህንነት አኳያ ከህዝብ ለሚቀርብ 2 ጥቆማ ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ 1 ሲከናን አፈጻጸሙ 50 % ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ሊል የቻለው የቀረበ ጥቆማ ባለመኖሩ ነው፡፡
- በዚህ ስድስት ወር ውስጥ 80 የተቀነባበረ መኖ ናሙና ለማሰባሰብ ለማካሄድ ታቅዶ 137(>100%) የተከናወነ ሲሆን፣ ሲሆን አፈጻጸሙ በጣም ከፍተኛ ሊሆን የቻለው ለስራው በቂ የበጀት ድጋፍ ከኤስ ኤን ቪ ፕሮጀክት በመገኘቱ ነው፡፡

**<u>በኢንስፔክሽን ግኝት ላይ የተወሰደ እርምጃ፡-</u>**

በአንድ የእንስሳት መኖ አስመጪ ድርጅት እስከሚወገድ ድረስ ተለይቶ እንዲቀመጥ ተደርጎ የነበረ የመኖ ግብአት የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት እንዲወገድ ተደርጓል፡፡ የተወገዱ ግብዓቶች፡-

- Dololayit-------6300 sachet,
- Resergen-----1997 sachet,
- Rminivt----------321battle/100ml,
- Floxivet---------22 litter,
- Aminovit powder--------3 sachet

- አንድ የእንስሳት መኖ አምራች ተቋም የምርት እና ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ እንደሌለው በመረጋገጡ ተቋሙ ጉድለቱን እስኪያሟላ ድረስ እንዲታገድ ተደርጓል፣
- በመኖ ናሙና ምርመራ ውጤት መሰረት በናሙናው የሚወከለውን መኖ ከገበያ እንዲያሰባስቡ በደብዳቤ ከተጠየቁ 6 መኖ አምራች ድርጅቶች መካከል፡-
- አንድ ድርጅት በገበያ ላይ ያሰራጨውን 10 ኩ/ል የጀማሪና 5ኩ/ል የቁብ መኖ አሰባስቧል፣
- 5 ድርጅቶ ምርቱ በጥቅም ስለዋለ ማሰባሰብ እንዳልቻሉ በጽሁፍ አሳውቀዋል፡፡
- 3 መኖ አምራች ድርጅቶ ቶክሲን ባይንደር (Toxin Binder) በሚያመርቱት መኖ ውስጥ የሚጨምሩና የውስጥ ጥራት ቁጥጥር SOP ያላቸው መሆኑን በክትትል ኢንስፔክሽን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ለ3 ድርጅቶች ቶክሲን ባይንደር ኢንዲጠቀሙ እና SOP እንዲያዘጋጁ በመስክ ግብረመልስ ተሰጥቷቸዋል፤

- አምስት (5) የመኖ ንግድ ተቋማት በኢንስፔክሽን ወቅት ስላልተገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሷቸው ተደርጓል፣
- ሁለት ተቋማት ለተቆጣጣሪዎች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እና በአዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀጽ 26 (1) ፊደል ተራ "ሀ" እና በመመሪያ ቁጥር 16/2010 አንቀጽ 29 እና 38 የተደነገገውን ድንጋጌ በመተላለፋቸው፣ ጉድለታቸውን ወይም ጥፋታቸውን እስኪያስተካክሉ ድረስ እንዲታገዱ ተደርጓል፣
- አንድ ተቋም የቦታ ለውጥ ሲያደርግ ለባለስልጣኑ አለማሳወቁ እና በተጓደለ ባለሙያ ሲሰራ በመገኘቱ፣ በመመሪያ ቁጥር 16/2010 አንቀጽ 29 የተጠቀሰውን ድንጋጌ የጣሰ በመሆኑ፣ ጉድለቱን እስኪያስተካክል ድረስ እንዲታገድ ተደርጓል፣

<u>የተከናወነ የመኖ መረጃ እና አቅም ግንባታ ሥራዎች፡-</u>

- በዚህ ስድስት ወራት የተመዘገበ የመኖ ንግድ ተቋም፣ ባለሙያ፣ መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መረጃዎችን 6 ጊዜ ለማደራጀት ታቅዶ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡

- በዚህ ግማሽ ዓመት በእንስሳት መኖ ንግድ ስራ ዘርፍ ለመሰማራት መረጃዎችን ለመውሰድ ለቀረቡ 30 ተገልጋዮች ተገቢውን መረጃ ለመስጠት ታቅዶ ለ30 አገልግሎቱን ፈልገው ለሚመጡ ተገልጋዮች መረጃ የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡

- በዚህ ግማሽ ኣመት ከ66 የመኖ ማምረቻ ተቋማት የምርት መረጃ ለማሰባሰብና ለማደራጀት ታቅዶ ከ 62 ድርጅቶች መረጃ ተሰባስቧል፡፡ አፈጻጸሙ 94% ነው፡፡

✓ **የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነትን ማረጋገጥ**

እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት በ80 የመኖ ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በ146 (>100%) የመኖ ምርት ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ፍተሻ ተግባራትን ማከናወን የተቻለ ሲሆን ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የጥራት ምርመራ ምርመራ ከተሰራላቸው 146 የመኖ ምርት ናሙናዎች ውስጥ 45.2% (66/146) የፕሮቲን ይዘታቸው ከተቀመጠው ስታንዳርድ በታች ሲሆን 10.95% (16/146)

የሚሆኑ የመኖ ምርት ናሙናዎች ደግሞ የፋይበር መጠናቸው ከሚፈለገው ስታንዳርድ በላይ እንደሆነ ለማውቅ ተችሏል።

- እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት በ 80 የመኖ ምርት ናሙናዎች ላይ የአፍላቶክሲን የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በ 116 (>100%) የመኖ ምርት ናሙናዎች ላይ ምርመራ ማካሄድ ተችሏል። የአፍላቶክሲን ምርመራ ከተሰራላቸው 116 ናሙናዎች ውስጥ በ 6.8% (10/146) የመኖ ምርት ናሙናዎች ላይ በስታንዳርድ ከተቀመጠው የሴፊቲ ስታንደርድ መጠን በላይ የአፍላቶክሲን መጠን የተገኘባቸው መሆኑን በላቦራቶሪ ምርመራ ማረጋገጥ ተችሏል። በዚህ ሩብ አመት በዕቅድ ከተያዘው የመኖ ምርት የናሙናዎች ላይ ምርመራ ማካሄድ የተቻለው በኤስ.ኤን.ቪ. (SNV) ፕሮጀክት ድጋፍ ተጨማሪ የመኖ ናሙናዎች ተሰብስበው ለላቦራቶሪ ምርመራ በመቅረባቸው እና ሥራውን ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ ጭምር የላቦራቶሪ ባለሙያዎች እንዲከናወን በመደረጉ ነው።

- የመኖ ማይክሮባዮሎጂካል ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎትን በተመለከተ በዚህ 2ኛ ሩብ ዓመት በ10 እስከዚህ ሩብ አመት በ20 የመኖ ምርት ናሙናዎች ላይ የማይክሮባዮሎጂካል ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 20 (>100%) ናሙናዎችን መመርመር ተችሏል። የማይክሮባዮሎጂ (ሳልሞኔላ እና ኢኮላይ ባክቴሪያ ልየታ) ምርመራ ከተሰራላቸው ውስጥ 5% (1/20) የመኖ ናሙና ላይ ብቻ የኢኮላይ ብክለት እንደለ ለማረጋገጥ ተችሏል።

**ምክረ-ሀሳብ፡** የመኖ ምርት ጥራት መጓደል የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ይቀንሳል፤የመኖ ደህንነት ችግር የእንስሳት ጤና እና በእንስሳት ምርት ደህንነት ጉድለት በሰው ጤና ላይ አደጋ ያስከትላል፤ የእንስሳት አርቢ ዜጎች ያላ አግባብ ተጨማሪ የገንዘብ ኪሳራ እንዲደርስባቸው ያደርጋል። በመሆኑም የመኖ ምርት ጥራትና ደህንነት እንዲሻሻል ቀጣይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ ይመከራል።

## 3.5 ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የዕጽዋት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት

✓ዓለም አቀፍ የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ ሥራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል ማዕከሉ ከዚህን በፊት እውቅና ወይም አክሪዲቴሽን ያገኘባቸውን 13 የምርመራ አይነቶችን (በፋርማስውቲካል፣በኬሚካልና በማይክሮባዮሎጂካል) በማስቀጠል ደረጃወን የጠበቀ የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ አገልግሎት ለመስጠት ተችሏል፤ዝርዝሩ እንዲሚከተለው ቀርቧል።

- በዚህ 2ኛ ሩብ ዓመት 9 ነባር የጥራት ማኔጅመንት መደበኛ የአሰራር ሰነዶችን ለመከለስ ወይም አዳዲስ ለማዘጋጀት ታቅዶ 7 (77.8%) መፈጸም ተችሏል። እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት 18 የተለያዩ መደበኛ የአሰራር ሰነዶችን/ፕሮሰጀሮችን ለመከለስ ዕቅድ ተይዞ 16 (88.9%) የጥራት ማኔጅመንት የአሰራር ፕሮሲጀሮችና ሌሎች አስፈላጊ ዶክመንቶች ተከልሰው ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

- በዚህ 2ኛ ሩብ ዓመት 5 የምርመራ ስነ ዘዴዎችን ተዓማኒነትና ትክክለኛነት ማረጋገጫ ቬሪፊኬሽን ወይም ቫልዴሽን ተግባራትን ለማከናወን ታቅዶ 2 በማይክሮባዮሎጂ የምርመራ ስነ ዘዴዎች ላይ ሥራውን ማከናወን ተችሏል። እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት 10 የላቦራቶሪ ምርመራ ስነ ዘዴዎች የትክክለኝነት ማረጋገጫ ሥራዎችን ለማከናወን በዕቅድ ከተያዙት ውስጥ 7 (70%) ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል። በላቦራቶሪ ምርመራ ስነ ዘዴዎች ትክክለኝነት ማረጋገጫ ግብዓት አቅርቦት እና የላቦራቶሪ መሳሪያ ብልሽት ጥገና መዘግየት ምክንያት 3ቱ ወደሚቀጥለው ሩብ አመት ተላልፏል። ይህ ሥራ የላቦራቶሪ የምርመራ አገልግሎት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግና ተጨማሪ የላቦራቶሪ ምርመራ ዕውቅና ለማግኘት የሚረዳ ወሳኝ ተግባር ነው።

- እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት ወይም 6 ወር (ግማሽ አመት) የላቦራቶሪ መሳርዎች ልኬት ትክክለኛነት ማረጋገጫ ለማሰራትና አለም አቀፍ የልኬት ትረሰብሊቲ ለማስጠበቅ የተያዘ ዕቅድ ባይኖርም 152 የተለያዩ የላቦራቶሪ ምርመራ ናሙና ማዘጋጃ ቮሉሜትሪክ ቁሳቁሶችና እና 27 መሳርያዎች በኢትዮያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት የልኬት ማስተካከያ ሥራ እንዲሰራላቸው በማድረግ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንድሰጡ ተደርጓል። ከዚህ ውስጥ በመጀመሪያ ዙር 2 የናሙና ቅዝቃዜ ሰንሰለት ማቆያ መሣሪያዎች (2 የላቦራቶሪ ፍሪጅ) እና 4 ግላስ ቴርሞሜትሮች ስታንደርድ የካሊብሬሽን መስፈርት ሳያሟሉ በመቅረታቸው በድጋሜ በኢትዮጵያ ስነ ልክ ኢንስትቲዩት ካሊብሬሽን እንዲሰራላቸው ተደርጓል።
- በላቦራቶሪ መሣሪያዎች ብልሽት ምክንያት ማዕከሉ የሚሰጣቸው የጥራት ምርመራ አገልግሎት ሥራዎች እንዳይቋረጡና እንዳይስተጓጉሉ እንዲሁም ለተቋሙ ሥራዎች የሚያስፈልጉ አዳዲስ የጥራት ምርመራ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች እንዲሟሉ ለማድረግ በርከታ ሥራዎች ተቅደው ተግባራዊ ተደርጓል፤ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

- በዚህ 2ኛ ሩብ ዓመት 20 የቅድመ ብልሽት መከላከልና የብልሽት ጥገና ሥራዎችን ለማከናወን ታቅዶ 4 የማይክሮባዮሎጂ ላቦራቶሪ መሣሪያዎች ላይ ብቻ ጥገና ማከናወን ተችሏል። እስከዚህ ግማሽ አመት (6 ወር) ለ 30 የላቦራቶ መሳሪያዎች የቅድመ መከላከልና የብልሽት ጥገና ሥራዎችን ለማከናወን ታቅዶ ለ 7 (23%) የላቦራቶሪ መሳርያዎች ብቻ ጥገና ለማሰራት ተችሏል። ለተቀሩት 23 የተለያዩ የላቦራቶሪ መሣሪያዎች የጥገና እና የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ለማሰራት በተባበሩት መንግስታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት እና በግብርና ሚ/ር የአደጋ ሥጋት ቅነሳ አካታችና የአርብቶ አደር ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮጀክት ድጋፍ የጥገና አገልግሎት ግዥ ጨረታ በሂደት ላይ ይገኛል።

- የማዕከሉን የጥራት ምርመራ አገልግሎት አቅም ለማሳደግ በዚህ 2ኛ ሩብ ዓመት 3 አዳዲስ የላቦራቶሪ መሣሪያዎችን ተከላ በማከናወን ወደ ሥራ ለማስገባት ታቅዶ የነበረ ሲሆን የ 2 (66%) (1 የመኖ እና 1 የመድኃኒት ምርት ጥራት ምርመራ) የላቦራቶሪ መሳርያዎች ተከላ በማጠናቀቅ ወደ ሥራ ለማስገባት ተችሏል። ተከላ የተከናወነላቸው መሣሪያዎች በግብርና ሚ/ር የአደጋ ሥጋት ቅነሳ አካታችና የአርብቶ አደር ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮጀክት ድጋፍ የተገዙ ሲሆን ማዕከሉ የሚሰጣቸው የጥራት ምርመራ የአገልግሎት መጠን እና አይነት ሽፋን አሳድጓል። ሌላው በዕቅድ ተይዞ የነበረው አንድ የማር ጸረ ተባይ ቅሪት ምርመራ መሣርያ እና ተጓዳኝ ቁሳቁሶች ግዥና ተከላ ያልተከናወነው በግብርና ሚ/ር የተቀናጀ የምግብ ሥርዓት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት ድጋፍ የግዥ ሂደቱ በመጓተቱ ምክንያት ነው።

- የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪዎች የምርመራ ብቃት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትና ተወዳዳሪነቱን ማሳደግና ማስቀጠል እንዲቻል ከተለያዩ አገራት የብቃት ማረጋገጫ የፍተሻ ናሙናዎችን በግዥና በድጋፍ በማስመጣት በማዕከሉ ሥር የሚገኙ 5 ላቦራቶሪዎች የፕሮፊሽንሲ መለኪያ ምርመራ ለማከናወን ችሏል። ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

- እስከዚህ 2ኛው ሩብ ዓመት የላቦራቶሪ የምርመራ ብቃት ማረጋገጫ ፍተሻ ናሙናዎችን ውጭ አገር ከሚገኙ ዓለም አቀፍ እውቅና ካላቸው የብቃት ማረጋገጫ ናሙና አቅራቢ ድርጅቶች በማስመጣት 16 ታቅዶ በ 19 (1 የመድኃኒት ፊዚኮ-ኬሚካል፣ 2 የመድኃኒት ማይክሮባዮሎጂ፣ 9 የሥጋ ምርት ማይክሮባዮሎጂ እና 7 የማር ፊዚኮ-ኬሚካል የጥራት መለኪያዎች) ላይ መሳተፍ ተችሏል። በተጨማሪም ከኦፊስ ኦፍ ቴክሳስ ስቴት ሶይል ሪሰርች በድጋፍ በተገኘ 1 የመኖ አፍላቶክሲን የምርመራ ብቃት ፍተሻ ናሙና ላይ ተሳትፎ በማድረግ አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል። ይህ አፈጻጸም የጥራት ምርመራ ማዕከል ላቦራቶሪዎች

እውቅና ባገኙባቸው የምርመራ አይነቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚያደርጋቸው የምርመራ የብቃት ደረጃ ላይ መገኘታቸውን ያረጋገጠ ተግባር ከመሆኑም በላይ በቀጣይ ማዕከሉ ለሚያደርጋው ተጨማሪ የሦስተኛ ወገን ዕውቅና ወይም አክሪዲቴሽን የማግኘት ጥረት ምቹ ሁኔታዎችን የፈጠረ ተግባር ውጤት ነው።

- አመታዊ የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት አሰጣጥ ክትትልና ምዘና ለማካሄድ በዚህ ሩብ አመት ታቅዶ የተከናወነ ሥራ ባይኖርም እስከዚ 2ኛ ሩብ አመት የኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት በማዕከሉ ተገኝተው ዓመታዊ የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ሥርዓት ትግበራ የክትትል ምዘና እንዲያከናውን ተደርጓል። በምዘናው ሂደት 4 ቀላል ግኝቶች የተለዩ እና 2 የማሻሻያ ቃል ምክረ-ሃሳቦች የተሰጡ ሲሆን ለነዚህ ግኝቶችና ምክረ ሃሳቦች የማስተካከያ ዕቅድ ተዘጋጅቶላቸው በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የማሻሻያ ሥራዎችን በአግባቡ በማጠናቀቅ ዝርዝር አፈጻጸሙን የሚገልጽ የሰነድ ማስረጃ ዎችንና ሪፖርት ለዕውቅና ሰጪው ተቋም ማቅረብ ወይም መላክ ተችሏል። የኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት የተሰራ የማሻሻያ ሥራ ውጤታማነት በማረጋገጡ ማዕከሉ ከዚህ ቀደም በ13 የላቦራቶሪ ምርመራ መመዘኛዎች ያገኘውን የሦስተኛ ወገን ዕውቅና ሙሉ በሙሉ እንዲቀጥል ወስኗል።

## የመረጃ አቅርቦት ሥርዓት እና አጠቃቀምን ማሻሻል

- የላቦራቶሪ መረጃዎችን የማደራጀት ሥራ ቀጣይነት ያለው ቢሆንም በዚህ ሩብ ዓመት እና እስከዚህ ግማሽ አመት የሚከተሉት የተቋሙ ዋና ዋና ቴክኒካል መረጃዎች በኤሌክትሮኒክስ ዳታ እና በሰነድ ተደራጅተው ለአገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል። ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል።
- የናሙና ቅበላና ምዝገባ እና ተያያዥ ሪፈራንስ ስታንዳርድ መረጃዎች፣ የምርመራ ሰርተፊኬቶች እና የብቃት ማረጋገጫ ናሙናዎች የምርመራ ውጤት መረጃዎች፣ ቴክኒካል የላቦራቶሪ ሥራ ሪከርዶች እና ተያያዥ መረጃዎች፣ ቋሚ እና አላቂ የላቦራቶሪ መሣሪያዎች፣የካሊብሬሽንና የጥገና አገልግሎት ዝርዝር መረጃዎች፣ የጥራት ማኔጅመንት ሰነዶች (የአሰራር መመሪያዎች፣ የምርመራ ስነ-ዘዴዎች፣የላቦራቶሪ የስጋት ማኔጅመንትና ትነተና ዝርዝር መረጃዎች፣ የውስጥና የውጭ ኦዲት ግኝቶች እና የጥራት ማኔጅመንት ሪቪው ሪፖርቶች)፣ ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ የማጣቀሻ ስታንዳርድ መጽሐፍት ወይም ፋርማኮፒያዎች እና የጋይድላይን መረጃዎች እንዲሁም የቴክኒካል ባለሙያዎች የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድ፣ የሥልጠና መረጃዎች

እና የሥራ መዘርዝር መረጃዎች በላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት መሰረት የማደራጀት ሥራ ተሰርቷል፡፡

- ዲጂታል የመረጃ አቅርቦት ስርዓት ለማሻሻልና መረጃዎችን ለባለሙያዎች እና ለአመራሮች ፈጣንና ተደራሽ ለማድረግ ጎግል ድራይቭ ሽት በመጠቀም ቋሚ እና አላቂ የላቦራቶሪ ግብዓቶች ቆጠራ እና ማቀናነሻ ገጽ፣ የላቦራቶሪ ግብዓት ግዥ ፍላጎት ማሳወቂያ፣ ስፔስፊኬሽን ማዘጋጃና መገምገሚያ ገጽ እንዲሁም የእንስሳት ምርትና ግብዓት ናሙናዎች የጥራትና ደህንነት ምርመራ ሥራዎች ሂደት መከታተያ ገጾች ተዘጋጅተው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡
- በተጨማሪም በዚህ በጀት አመት ውስጥ በግብርና ሚ/ር ድራይቭ ፕሮጄክት የበጀት ድጋፍ እና የአይሲቲ ዲፓርትመንት ቴክኒካል እገዛ ለማዕከሉ ዘመናዊ የላቦራቶሪ ኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ሥርዓት ዝርጋታና የተቋሙን ዳታ ወይም መረጃ ማኔጅመንት ስርዓት ዲጂታላይዝ ለማድረግ የሚረዳ አማካሪ/ኮንሰልታንት ቅጥር ለመፈጸም የሚያስችል የጨረታ ሥራ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

**የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት ደረጃ ማሳደግ እና ማሻሻል**

- እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት ለማዕከሉ ሥራ የሚያስፈልጉ ቋሚና አላቂ የላቦራቶሪ ግብዓቶች የግዥ ፍላጎት የመለየትና 4 የግዥ ስፔስፊኬሽን ሰነዶች የማዘጋጀት ተግባራት ማከናወን የተቻለ ሲሆን ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በመደበኛ በጀት የሚገዙ አላቂ የላቦራቶሪ ግብዓቶች ተለይቶው በመንግሥት የኤልክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት (e-GP) ግዥ ለመፈጸም የሚያስችል ጨረታ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በግብርና ሚ/ር የአካታችና አደጋ ሥጋት ቅነሳና የአርብቶ አደር አከባቢ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮጄክት ድጋፍ አለም አቀፍ ጨረታ አሸናፊ በሆኑ ሁለት አቅረቢ ድርጅቶች አማካኝነት ለማዕከሉ የተገዙ ቋሚ እና አላቂ የላቦራቶሪ ግብአቶችን በተጠየቀው ቴክኒካል የግዥ ፍላጎት መግለጫ መሰረት መሆኑን በማረጋገጥ ገቢ ተደርገው ለአገልግሎት እንዲውሉ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል፡ :

- የማዕከሉን የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት ለማሻሻል የኢትዮ ፓንደሚክ ፈንድ ፕሮጄክት ትግበራ አስተባባሪ ለሆኑት የዓለም ጤና ድርጅት (WHO) በ 874,923.00 የአሜሪካን ዶላር 177 ልዩ ልዩ የላቦራቶሪ ግብዓቶች ግዥ እንዲሁም በዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት (FAO) በ 807,585.40 የአሜሪካን ዶላር 125 የተለያዩ የላቦራቶሪ ግብዓቶችን በመለየት ዝርዝር የግዥ መግለጫ ወይም ስፔስፊኬሽን ሰነድ በማዘጋጀት ግዥው በልማት አጋር ድርቶቹ በኩል ተፈጽሞ ለማዕከሉ እንዲቀርብ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

- በዓለም ጤና ድርጅት (WHO) የኢትዮ ፓንደሚክ ፈንድ ፕሮጀክት ድጋፍ 25 ዘመናዊ ላብቶፕ እና 10 ዴስክቶፕ ኮምፒውተሮች ከነ ሙሉ አክሰሰሪያቸው በ 55,125.00 የአሜሪካን ዶላር (8 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ) ግዥ ተፈጽሞ ለማዕከሉ ገቢ ተደርጎ ለአገልግሎት እንዲውል ተደርጓል፡፡

- ማዕከሉ የላቦራቶሪ ግብዓት ማከማቻ እና በቀላሉ በሙቀት የሚበላሹ ሪኤጀንቶች የቅዝቃዜ ሰንሰለት ማስጠበቂያ ወይም ማቆያ መጋዝን የግንባታ ዲዛን አሰርቶ ለግብርና ሚ/ር ድራይቭ ፕሮጀክት የበጀት ድጋፍ ጥያቄ መሰረት ፕሮጀክቱ ለመጋዘን ግንባታ የሚያስፈልገውን በጀት በመፍቀድ የግንባታ ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል የግዥ ቅድመ ሆኔታዎችን በማመቻቸት ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

- የእንስሳት ጥራት ምርመራ ማዕከል ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ምንም አይነት እድሳትና ጥገና ያለተሰራለት በመሆኑ በሥራ ላይ ከፍተኛ የሆነ ችግር አስከትሏል፡፡ ችግሩን ከመሰረቱ ለመቅረፍ እንዲቻል ከጥራት ምርመራ ማዕከል፣ከግብርና ሚ/ር እና ከብሔራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የተውጣጡ መሃንድሶችንና ቴክኒካል የባለሙያዎች ቡድን በማቋቋም አጠቃላይ ለማዕከሉ እድሳትና ጥገና የሚደረግላቸውን ችግሮችን አይነትና መጠን የመለየት፣ልኬት እንዲሰራቸው የማድረግ፣ የእድሳትና ጥገና የዋጋ ግምት (Bill of Quantity) እና የጥገና አገልግሎት ግዥ የጨረታ ሰነዶችን በማደራጀትና በማዘጋጀት በግብርና ሚ/ር የምግብ ስርዓት መጠናከሪያ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የበጀት ድጋፍ የጥገና አገልግሎት ግዥ በጨረታ አሸናፊ ተቋራጭ አማካኝነት ለማዕከሉ አጠቃላይ እድሳትና ጥገና እንዲደረግለት በማድረግ ለተቋሙ ሰራተኞች ምቹ የሥራ ከባቢ ለመፍጠር እንዲሁም ማዕከሉ ለሚያከናውናቸው የጥራት ምርመራ አገልግሎት አሰጣጥ ተስማሚና ደረጃወን የጠበቀ እንዲሆን በርካታ ተግባራት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

**የአመራርና ፈጻሚ አካላት አቅም መገንባት**

- የማዕከሉን የአገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት ለማሳደግ እንዲሁም የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ለማጠናከር የተለያዩ የአቅም ግንባታ እና የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥልጠናዎችን ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

- በዚህ 2ኛ ሩብ ዓመት የምግብ ወለድ በሽታ መከላከል፣መለየትና አፋጣኝ ምለሽ መስጠት ለሚችሉ ግንባር ቀደም የእንስሳት፣የሰው እና የዕጽዋት ጤና ቁጥጥር ባለሙያዎችን የሥልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በ12 ክልሎች እና 2 ከተማ አስተዳደሮች ላይ ተካሄዷል፡፡ የተሰበሰበውን መረጃ በመተንተን በባለድርሻ አካላት የምክክር አውደ ጥናት በማስተቸት ዋና ዋና የሥልጠና ፍላጎት ለመለየት ተችሏል፡፡ ለተለዩት የሥልጣና ፍላጎት ወጥነት ያለው የሥልጠና ማኑዋል ወይም ሞጁል በማዘጋጀት በቀጣይ የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥልጠና ለግንባር ቀደም ባለሞያዎች በመስጠት የምግብ ወለድ በሽታ የሚያስከትለውን ጉዳት አስቀድሞ ለመከላከል፣ ለመለየትና ፈጣን ምላሽ ለማስጠትና ብሎም የተቋሙን አገራዊ የአገልግሎት ሽፋን ለማሳደግና ችግሩን ለመቅረፍ እንዲቻል በዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት የኢትዮ ፓንደሚክ ፈንድ ፕሮጀክት ድጋፍ ከተለያዩ ተቋማት ለተውጣጡ 40 ባለድርሻ አካላት (33 ወንድ እና 7 ሴት) የምክክር አውደ ጥናት ላይ በማሳተፍ ለሥልጠና ማኑዋል ዝግጅት የሚረዳ ጠቃሚ የማሻሻያ ምክረ ሀሳብና ግብዓት ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡
- እስከዚህ 2ኛ ዓመት ድረስ አግባቢነት ባላቸው የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለ 220 ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ 256 (>100%) ተሳታፊዎች የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ ዝርዝሩ እንዲሚከተለው በሰንጠራዥ ውስጥ ቀርቧል፡፡

*ሠንጠራዥ፡ የባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት አቅም ግንባታ ሥራዎች ማጠቃለያ ሪፖርት*

| ተ/ቁ | የሥልጠና/ምክክር አውደ ጥናት ርዕስ | **ወ** | **ሴ** | **ድምር** |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ድጋፍ ሁለት ከፍተኛ ባለሙያዎች ዓለም አቀፍ የላቦራቶሪ ጥራት አስተዳደር ስርዓትና የአክሪዲቴሽን ብቃት ምዘና ላይ የንድፈ ሀሳብ እና የተግባር ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል | 2 | 0 | 2 |
| 2 | በዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት (FAO-EPPR) የፓንደሚክ ፈንድ ፕሮጀክት ድጋፍ የምግብ ወለድ በሽታ መከላከል፣ መለየትና ፈጣን ምላሽ መስጠት የሥልጠና ፍላጎት መለየት የዳሰሳ ጥናት ላይ ከፌዴራል መ/ቤት ከተውጣጡ ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር አውደ ጥናት ወይም ቫልዴሽን ማካሄድ ተችሏል | 33 | 7 | 30 |
| 3 | በግብርና ሚ/ር ዲራብይ (DRIVE) ፕሮጀክት ድጋፍ በባለሥልጣን መ/ቤቱ የሁለቱም ሬጉላቶሪ ዘርፍ ለሚገኙ የላቦራቶሪ፣ መግቢያ እና መውጫ ኬላዎች እና የፍተሻ ጣቢያዎች እና ሌሎች የኢንስፔክሽን ሥራዎች ላይ ለሚሰሩ ባለሙያዎች በሥነ-ሕይወታዊ ደህንነት እና ጥበቃ (Biosafety & Biosecurity) ላይ የንድፈ ሃሳብ ሥልጠና መሥጠት ተችሏል | 72 | 40 | 112 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4 | በተባበሩት መንግስታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት (UNIDO) ድጋፍ ከፌደራል እና 17 የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች ለተውጣጡ ባለሙያዎች በእንስሳት ምርት ጥራት እና ደህንነት እንዲሁም የሥጋ ምርት የመድኃኒት ቅሪት ምርመራ ሥነ-ዘዴዎች ላይ የንድፈ-ሃሳብ እና የተግባር ሥልጠና መስጠት ተችሏል | 28 | 2 | 30 |
| 5 | በግብርና ሚ/ር ድራይቭ (DRIVE) ፕሮጀክት ድጋፍ በባለስልጣን መ/ቤቱ በሁለቱም የሬጉላቶሪ ዘርፍ ለሚገኙ እና በምግብ ጥራት እና ደህንነት ዙሪያ ለሚሰሩ ባለሙያዎች እና አመራሮች በምግብ ጥራት እና ደህንነት እንዲሁም የብሔራዊ፣ ቀጠናዊ፣ ዓለም-አቀፋዊ የቁጥጥር ሥርዓቶች፣ፕሮቶኮሎች እና ተያያዥ ርዕሰ-ጉዳዩች ላይ የንድፈሃሳብ ስልጠና መሥጠት ተችሏል | 47 | 33 | 80 |
| 6 | በዓለም አቀፍ የኢንሴክት ስነ-ሕይወታዊ እና ኢኮሎጂ ጥናት ማዕከል (ICIPE) ድጋፍ ሁለት የላቦራቶሪ ባለሙያዎች በኬንያ ናይሮቢ የማር ጥራት እና ደህንነት ምርመራ ዘዴ ላይ የንድፈ-ሃሳብ እና የተግባር ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል | 1 | 1 | 2 |
| | **ድምር** | **183** | **83** | **256** |

***ድጋፍ ማፈላለግ እና የሃብት ምንጭ ማሳደግ/ማበራከት***

- ***ፓንደሚክ ፈንድ* (FAO and WHO):** የሰው ኃይል አቅም ግንባታ፣ የላቦራቶሪ አቅም ግንባታ እና የምግብ ጥራት እና ደህንነት እንዲሁም የጸረ-ተህዋስያን በጀርሞች መለመድ ደሰሳ ጥናት፤
- **በግብርና ሚኒስቴር ለድራይቭ ፕሮጀክት:** የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ጥገና፣ የቀዝቃዛ ክፍል ግንባታ፣ የላቦራቶሪ ኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ሥርዓት ዝርጋታ፣ የላቦራቶሪ ምርመራ ሥራ ትክክለኛነት ማረጋገጫ ናሙናዎች ግዥ እና በውጭ ሃገር የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለማግኘት የሚያስችል ፕሮፖዛል ቀርቧል፤
- **የምግብ ሥርዓት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት:** የማር ጥራትና ደህንነት ምርመራ ስራ ለማካሄድ የሚረዱ የመሣሪያዎች ግዥ፣የላቦራቶሪ ጥራት ማረጋገጥ ሥራዎችን ለመደገፍ፤
- **በተባበሩት መንግስታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት** የልማት ድጋፍ ላቦራቶሪው ሲያካሄድ የነበረውን በስጋ ናሙና ውስጥ የእንስሳት መድኃኒት ቅሪት ምርመራ ስራን በዓይነት እና በመጠን ለማሳደግ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ይገኛል:: በዚህም የጥራት ምርመራ ስራዎችን ለማካሄድ የሚያግዙ ዘመናዊ መሳሪያዎችን የቅደመ-ብልሽት፣ የብልሽት ጥገና ድጋፍ፣ የሰውኃይል ስልጠና ድጋፍ እና ሶስት ዓይነት የተለያዩ የምርመራ ስነ-ዘዴዎችን

ቫሊዳት ለማድግ እና ዘዴዎቹን ለማልማት የሚያስችሉ የቴክኒክ ድጋፎችን የሚያስገኙ ፕሮፖዛሎች ተዘጋጅተው ወደ ትግበራ ገብተዋል፡፡

**ቅንጅታዊ አሰራርን ማሻሻል እና ማጠናከር**

ማዕከሉ ከመንግስታዊ ተቋማት እና ከዓለም አቀፍ የልማት አጋር ድርጅቶች ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር በዚህ ሁለተኛው ሩብ ዓመትም ተቋማዊ ትብብርና ስትራቴጂካዊ አጋርነትን በማጠናከር የተለያዩ ተግባራት አከናውኗል፡፡ የሚከተሉትን ተጠቃሽ ናቸው፡-

- የአሰራር ሥርዓት ማሻሻል፡ ከመድኃኒት ሬጉላቶሪ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ጋር በመቀናጀት፣ ወጪ ቆጣቢና በሥጋት ላይ የተመሰረተ (Risk-based) የምርመራ መምሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ አሰራር የምርመራ ሂደቱን ይበልጥ ውጤታማና የተቀላጠፈ ያደርገዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡
- የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን፡ የላቦራቶሪ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት (LIMS) ለመዘርጋት ከግብርና ሚኒስቴር የአይሲቲ ባለሙያዎች ጋር የጋራ ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ለዲራይቭ (DRIVE) ፕሮጀክት ቀርቧል፡፡ በአሁኑ ወቅት ዝርጋታ የሚያከናውን አማካሪ ድርጅት የጨረታ ግዥ ሥራ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡
- የሰው ኃይል ልማት፡ ከባለሥልጣኑ የሰው ሀብት ልማትና ስትራቴጂክ ጉዳዮች መሪ ሥራ አስፈጻሚዎች ጋር በመተባበር የተቋሙን የ10 ዓመት የሰው ኃይል ልማት ፍላጎትና ዕቅድ የማዘጋጀት ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡
- ዓለም አቀፍ የላቦራቶሪ ትስስር፡ ከአፍርካ ህብረት የእንስሳት ክትባት ቁጥጥር ማዕከል (AU-PANVAC) ጋር በተፈጠረው የሥራ ትስስር የክትባት ጥራት ምርመራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡
- የአቅም ግንባታና ተሞክሮ ልውውጥ፡ ከዓለም አቀፍ አአቶሚክ ኤጅንሲ እና ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለስልጣን በትብብር በተዘጋጀ ሥልጠና አንድ ባለሙያ በመገኘት በላቦራቶሪ ብቃት ፍተሻ (PT) ላይ የአቅም ግንባታና ተሞክሮ ልውውጥ እንዲወስድ ተደርጓል፡፡ ይህም የተቋሙን የላቦራቶሪ ጥራት የማረጋገጥ አቅም ይገነባል ተብሎ ይጠበቃል፡፡
- ማህበራዊ ኃላፊነትና ድጋፍ፡ የምርመራ ፋይዳቸውን ያጠናቀቁ እና ጥራታቸው የተጠበቀ የእንስሳት መድኃኒት ናሙናዎች፣ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ የእንስሳት ሕክምና ትምህርትና አገልግሎት እንዲውሉ በድጋፍ መልክ ተሰጥተዋል፡፡

**የማዕከሉን ክትትልና ግምገማ፣የድጋፍና ግብረ መልስ አሰራርን ማጎልበት**

- የማዕከሉ የአመት እቅድ፣ የ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት ዕቅድ ክንውን ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ ክፍል ማቅረብ ተችሏል፡፡ የማዕከሉ ዕቅድ ተፈጻሚ እንዲሆን አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በመስጠት የሩብ ዓመት ዕቅድ ተፈጻሚ እንዲሆን ብርቱ ጥረት ተደርጓል፡፡

**ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ**

- ✓ ባለፉት ስድስት ወራት የ4 የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ብቃት በኢንስፔክሽን ለማረጋገጥ ታቅዶ ተከናውኗል፡፡ ይህም የመጨረሻ ግምገማ የተካሄደባቸውን መመሪያዎች መስፈርት በመጠቀም በተደረገ የሙከራ ኢንስፔክሽን 2 የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት፣ 1 የግብርና መሳሪያ ገጣጣሚ ድርጅት እና 1 የግብርና መሳሪያ አስመጪ ድርጅት፤ በድምሩ 4 ድርጅቶች ብቁ መሆናችውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ሆኗል፡፡

4 ታቅደው ያልተከናወኑ ሥራዎች ከነምክንያታቸው

- የማር እና ሥጋ ኬሚካል ቅሪት የምርመራ ሥራዎች በላቦራቶሪ መሳሪያዎች ብልሽት ምክንያት
- የምርመራ ስነ-ዘዴ ቅቡልነትና ተዓማኒነት ማረጋገጫ (Test method validation) ተግባራት ለማከናወን የሚያስፈልጉ የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት ግዥ መጓተትና ተደራራቢ ሥራዎች በመብዛታቸው ምክንያት አልተሰራም፡፡
- የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ጥገና መለዋወጫዎች እና የጥገና አገልግሎት ግዥ በበጀት እጥረት ምክንያት አልተከናወኑም፡፡

- ✓ በዚህ ግማሽ ዓመት ለአንድ (1) የግብርና ምርምር/ኤክስቴንሽን/ ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ አልተከናወነም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የቁጥጥር ስራው ለማስጀመር የተዘጋጁ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያዎች ባለመጽደቃቸው ነው፡፡

## 5 ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

በባለስልጣኑ ሴቶችን እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ እና የማህበራዊ አካቶ ትግበራን በማሻሻል ምቹ አካባቢ በመፍጠር በቁጥጥር ሥራው ላይ የተሻለ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ይቻል ዘንድ ቀጣዮቹ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

**የሴቶችን አቅም በመገንባትና እኩል ተጠቃሚነታቸውን በማሳድግ ለቁጥጥር ተግባሩ ያላቸውን ሚና ማጉለበት**

- የሥርዓተ-ፆታ ማካተት፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና የሰብአዊ መብት ጥሰት በ በጥቅሉ 7 የስራ ክፍሎች እና ቅርንጫፍ ጋር በመከናወኑ አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡
- የሥርዓተ-ፆታ ማካተትና ጾታዊ ትንኮሳ ስልጠና በድሬደዋእና በሃዋሳ ጣቢያ ወንድ 62 ሴት 27 ስልጠና የተሰጠ ሲሆንአፈጻጸሙ 100% ነው፡፡
- የአመራርና ውሳኔ ሰጪነት ስልጠና ለ 50 ስልጠና የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙም(100%) ነው
- እንደ ተቋም በቀን ታህሳስ 2/2018 ዓ.ም በኤች.አይቭ ኤድስ ነጭ ሪቫን ቀን አጠቃላይ በሴቶች ጥቃት እናተጋላጭ የህብርተሰብ ክፍሎች ዙሪያ ለግንዛቤ ተሰጧል ይህም አፈጻጸሙ 100% ነው

**በባለስልጣኑ የሴቶች፣ህጻናት፣ወጣቶችና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ**

- ለሁለት(2) አደጋ ተጋላጭ ህፃናት 6275 ብር ለእያንዳንዳቸው አጠቃላይ 12550 ብር ድጋፍ ተደርጓል፡፡

- የሴቶችና የወጣቶች ኔትወርክ ማስፋፋት የሚል አንድ(1)ታቅዶ የመልክት ሰራተኞች በወረቀት እና መሰል ነገሮችን በመሰብሰብ እየሠሩ ቢሆንም የገቢ ምንጮችን ለማስፋት የፎቶ ኮፒ፣ የፕሪንተር እና የእስቴሽነሪ ስራ ላማስጀመር የቢዚነስ ፕላን የተዘጋጀ ሲሆን ወደ ስራ ለመግባት ዝግጅት ላይ ነው
- የህፃናት ማቆያ ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችና ህፃናት ክትትልና ድጋፍ በየጊዜው እየተደረገ ሲሆን አስፈላጊ ቁሳቆሶችን በማሟላት እና የማብሰያ፣የጽዳት ቦታቻዎን ማመቻቸት ስራ ተከናዎኗል ይህም አፈጻጸሙ 100% ነው
- በቅጥር፣ በደረጃ እድገት፣ በስልጠናና በዝውውር ወቅት ፍትሃዊ አሰራሮች የተከታተል ሲሆን ዝውውር በግል ጥያቄ የተደረገ ስለሆነ ውድድር የለውም አዎንታዊ ድጋፍ የለም ፡- የተወዳዳሩት ተመሳሳይ ፆታ በመሆናቸው በመሆኑም አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡

- ለተማሪዎች (ከ1-4)ተኛ ክፍል 206 የትምህርት ቁሳቁስ ( የእንግሊዝ፣የሂሳብ እና የአካባቢ ሳይንስ አጋዥ መጽሃፍ) ለገጣፎ ክ/ከተማ ጣፎ ወረዳ ለወርገኑ ት/ቤት ድጋፍ ተደርጓል ይህም አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡
- ለ200 የተቋሙ ሰራተኞች የHIV/AIDS ስልጠና መስጠት የሚል ታቅዶ ለ80 ሴት እና ለ120 ወንድ ሰራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰቷል ይህም አፈጻጸም 100% ነው
- 15 ዩኒት ደም ለመለገስ ታቅዶ 20 ዩኒት ደም ከተቋሙ ሰራተኞች የተሰበሰበ ሲሆን አፈጻጸሙም 100% ነው
- 2 የአቅመ ደካማ ቤት ግንባታ ማስተባበር የታቀደ ሲሆን ብር 8,000,000.00( ስምንት ሚሊዮን ) ተሰብስቦ ከግብርና ሚኒስር ጋር በጋራ እየተከናወነ በመሆኑ አፈጻጸሙም 100% ነው
- አንድ ጊዜ ለተቋሙ ጣቢያ ሴት ሰራተኞች ድጋፍ ና ክትትል የሚል ታቅዶ ለሃዋሳ ጣቢያ ሴትሰራተኞች ድጋፍና ክትትል የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙመ 100% ነው

**የማህበራዊ አካቶ ትግበራን በአካባቢ እና ማህበራዊ ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ለመቀነስ ተግባራዊነቱን መከታተል**

- አምራች ድርጅቶች ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንፃር በባህላዊ እሴቶች፣ቅርሶች፣ ወጎችና ልምዶች እንዲጠበቁ፤ የሰራተኞች ጤንነትና ደህንነት፣ የስራ ስምሪት መብትና የስራ ቦታ ሰላማዊ ግንኙነት መፍጠር የሚያስችል አሰራር እንዲዘረጉ፣ የአካባቢው ማህበራሰብ ተጠቃሚነትና መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር 10 የመኖ አምራች ተቋማትን ከመኖ ሪጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈጻሚ ክፍል ጋር በመሆን ክትትልና ድጋፍ ስራ ተከናውኗል አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡

ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ

- ✓ ባለፉት ስድስት ወራት የ4 የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ብቃት በኢንስፔክሽን ለማረጋገጥ ታቅዶ ተከናውኗል፡፡ ይህም የመጨረሻ ግምገማ የተካሄደባቸውን መመሪያዎች መስፈርት በመጠቀም በተደረገ የሙከራ ኢንስፔክሽን 2 የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት፣ 1 የግብርና መሳሪያ ገጣጣሚ ድርጅት እና 1 የግብርና መሳሪያ አስመጪ ድርጅት፤ በድምሩ 4 ድርጅቶች ብቁ መሆናችውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ሆኗል፡፡

6. የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል

የሰው ሀብት ሙሌት ፍላጎት መረጃ መሰብሰብ

- ➢ እስከዚህ ሩብ አመት የሰው ሀብት ሙሌት ፍላጉት መረጃ መሰብሰብ 1 ታቅዶ1 100% ተከናውኗል ፡፡
- ➢ እስከዚህ ሩብ አመት በተሰበሰበ መረጃ መሰረት የቅጥር ፍላጎት ትንተና መሥራት 1 ታቅዶ 1 በማከናወን 100% ተፈፅሟል፡፡
- ➢ በዚህ 6 ወር በተደረገው ዳሰሳ ጥናት መሠረት ክፍት የስራ መደቦችን በሰው ኃይል ማሟላት ታስቦ ለ7 ሰዉ በቅጥር ለ1 ሰዉ በዝውውር ተከናዉኛል ፡፡
- ➢ በዚህ 6 ወር ሠራተኞች ከጡረታ ማስከበር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራትን ለማከናወን ታቀዶ ለ8 ሠራተኞች የጡረታ መውጫ ጊዜ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው በማድረግ 100% ተከናውኗል፡፡

**የሠው ሀይል አቅም መገንባት**

- ✓ እስከዚህ ሩብ ዓመት የሰው ኃይል አቅም ክፍተት ለመለየት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድና የቅድመ ስልጠና መስኮችን መለየት፣ማቀድና በጀት መያዝ 1 ታቅዶ የቅድመ ስልጠና መስኮች የመለየት ስራ 100% ታቅዶ ተከናውኗል፡፡
- ✓ እስከዚህ ሩብ ዓመት በተለያየ ዘዴ የመፈጸም አቅምን ለማዳበር የሚያስችሉ ትምህርትና ስልጠናዎችን ማመቻቸት፣መከታተልና መደገፍ 100% ታቅዶ ተከናውኗል፡፡
- ✓ እስከዚህ ሩብ አመት ከሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ በተገኙ የረጅም ጊዜ የስልጠና እድሎች በ1 የትምህርት መስኮች የእጩ ሰልጣኞች ምዝገባ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የመረጃ አያያዝ እና አስተዳዳር ስርዓትን ማሳደግ

- ✓ በ6ወር ዉስጥ በተለያዩ ዘዴዎች የሚቀርቡ የማስረጃ ጥያቄዎችን 100 ለማስተናገድ ታቅዶ ተከናውኗል፡፡
- ✓ በ6 ወር ለ6 ጊዜ የሰራተኞችን መረጃዎች፣ በኮምፒዩተር ሲስተም መዝግቦ ማደራጀት ፣ የመረጃ ቋቱን የመከለስ ሥራ ታቅዶ 6ጊዜ በማከናወን 100% ተከናውኗል፡፡
- ✓ በ6 ወር ወጪና ገቢ ደብዳቤዎችን ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ተደርጋል ፡፡
- ✓ የሪከርድና ማህደር አደረጃጀትና አገልግሎት አሰጣጥ በማሻሻል የማህደሮችን እንቅስቃሴ መቆጣጠር 100% የተከናወነ ሲሆን ለሠራተኞች ማህደር የሚያገለግል ህትመት ጥያቄ ቀርቧል፡ :

**የሰራተኛ እርካታን በመጨመር ተነሳሽነትን ማሳደግ**

- ✓ በ6 ወር ዉስጥ የሙያ ደህንነትና ጤንነት የደንብ ልብስ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት የሠራተኞችን ጥቅማጥቅም በአግባቡ እየደረሰ መሆኑን መከታተል ተችሏል ፡፡

- ✓ እስከዚህ ሩብ አመት  የቅሬታና የዲሲፕሊን ኮሚቴ እንዲቋቋም በማድረግ ጉዳዮች ላይ ክትትል የማድረግ ስራ 100% ተከናውኗል፡፡

**የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ሪፖርት ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ-መልስን ማሻሻል**

**በ2ኛ ሩብ አመት ፣ የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ሪፖርት ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ-መልስን የማሻሻል ሥራ በዕቅዱ መሠረት ከተከናወኑ ተግባራት መካከል፡-**

- ✓ የ2016-2018 ዕቅድ ክንውን (የ3) ዓመት የሪፖርት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- ✓ የ2018 ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡
- ✓ የተቋሙን አመታዊ እና ሩብ አመት ሪፖርት ማደራጀት ማስገመገም እና ለሚመለከተው አካል በወቅቱ መላክ በሀርድና በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡ በስራ ክፍሉ የመረጃ ቋትም እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ ከነዚህም መካከል  ፣የ3 ዓመት እቅድ ፣የ3 ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት፣ የ2018 ዓመታዊ እቅድ፣የ2018 1ኛ ሩብ አመት ሪፖርት፣የ2018 ዓመታዊ የፕሮግራም በጀት ሪፖርትናየ2018 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት የድርጊት መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡

**ክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ መሆኑን ክትትል በማድረግ ለመደገፍ ቀጣዮቹ ክንውኖች ተፈጽመዋል፡፡**

- ➢ በ2ኛ ሩብ አመት  የተቋሙን አፈፃፀም ክትልና ግምገማ በማካሄድ ክፍትት የለየ ድጋፍ የማድረግ ስራ ለመስራት ቅድመ ሁኔታዎች ተዘጋጅቷል፡፡
- ➢ በ2ተኛ ሩብ አመት የተቋሙን የበጀት አፈጻጸም ክትትል በማድረግ በጀቱ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን መከታተል ለታለመለት ስራ መዋሉን ክትትል እና ድጋፍ የማድረግ ስራ ተሰርታል ፡፡
- ➢ የክትትልና ግምገማ ለማድረግ የተቋቋመውን ኮሚቴ በማጠናከር የባለስልጣኑን የዕቅድ አፈጻጸም ስርዓት ለማሻሻል የሚረዱና ተቋሙ ያለበት ደረጃ ለመመዘን የሚያስችል ቼክሊስት ተዘጋጅቶ ለክንውን ዝግጁ ተደርጓል፡፡ 50% ተፈፃማል ፡፡
- ➢ እስከዚህ ሩብ አመት ለባለስለጣኑ የሚመደበውን የመንግስት መደብ በየኘሮግራሙ በውጤት መደልደል እና አፈጻጸሙን የመከታተል ስራ ተሰርቷል፡፡
- ➢ ለ2019-2021 በጀት ዓመት የ3 ዓመት የፕሮግራም በጀት ዕቅድ ቅድመዝግጅት ማለትም የ በጀት ታጊንግ ሜይንስተሪሚንግና ቅድመትንበያ ስራዎች ተከናውነው ለሚመለከተው ተልኳል፡፡

**አጋትነት እና ሃብት ማሰባብሰብ**

- ➢ እስከዚህ ሩብ አመት ለባለስልጣኑ የሚመደበውን የመንግስት በጀት በየኘሮግራሙ በውጤት የመደልደል እና አፈጻጸሙን የመከታተል ስራ ተሰርታል ፡፡

- እስከዚህ ሩብ አመት በFSRP project ለባለስልጣኑ የተመደበውን በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋላቸውን በመከታተልና በመገምገም ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማድረግ ስራ ተሰርታል ፡ ፡
- በ2ተኛ ሩብ አመት በዕቅድ የተዘውን የባለድርሻ አካላት መድረክ የማዘጋጀት ስራዎች ተከናውነው በአመራሮች የስራ መደራረብ የተነሳ መድረኩ ወደ ሶስተኛው ሩብ አመት እንዲዛውር የማመቻቸት ስራ ተከናውኗል፡፡

**ዶክመንት ዝግጅት እና መረጃ አያያዝን ማሻሻል**

- የባለስልጣኑን የእቅድ እና በየሩብ አመቱ የሚከናወኑ አፈጻጸሞችን በሲስተም ለሚመለከተው አካል የማድረስ ስራ ተሰርቶል፡፡
- 2ተኛ ሩብ አመት የተቋሙን የአፈፃጸም ፕሮግረስ በየጊዜው በዌብ ሳይት እና በተለዩ ሚዲያዎች በመጠቐም ለህብረተሰብ ተረዳሽ ለማድረግ የማጥራት ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

**ሊሎች የተከናወኑ ስትራቲጂክ ስራዎች**

- የ Indicator Reference guideline በመጨረሻዉ ረቂቅ ላይ ግምገማ ላይ ተሳትፎ ተደርጎ አስተያየት ተሰጥቷል ፡፡
- በግበርና ሚንስተር አስተባባሪነት በተዘጋጀዉ የመረጃ ፍሰት ስርአቱ የማሻሽል የመተግበራ መስተዋወቂያ ላይ ተሳትፎ ተደርጋል የባለስልጣኑ የመረጃ ፍሰት ስርአት ለመገባት በእቅድ እዲካተት ተደርጋል ፡፡
- የፋይቶ ሳኒታሪ ስትራቴጂክ ፕላን ዝግጅትና የማፅዳቅ ሂደት ላይ በመገኘት የስትራቴጅክ ፕላኑን ማሻሻያና መስፈጸማ ስልቶች ላይ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡
- የእንስሳት ምርትና ግበዓት ጥረት ምርመር ላብላቶሪ ባዘጋጀዉ የምግብ ደንነትና አለም አቀፍ ህግጋት ስልጠና ላይ ተሳትፎ ተደርጋል ፡፡
- በአዲስ አበባና ዙራዋ በፓይላት ደረጃ እዲሰራ የተሰበዉ ስራ በፕሮጀክት መልክ እዲከናዎን በፕሮጀክት ዝግጅት ላይ ተሳትፎና የማስተባበር ስራ ተከናዉኗል ፡፡
- የክትትልና ግምገማ ሰነድ ግምገማና የምስክ ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት ለባለስልጣኑ መሪ ስራ አስፈጻሚዎችና ስራአስፈጻሚዎች ቀርቦ ተገምግሟል፡፡
- የሰዉ ሃብት ልማት የ5 አመት እቅድ እዲዘጋጅ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ላይ በርካታ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡
- በጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት የዕቅድ ዝግጅትና ካስኬዲንግ ስራ ተከናውኖ ለሚመለከተው አካል ተልኳል፡፡

- በDHIS tool ተግባራዊነት ላይ ከሚመለከታቸው የHISP Ethiopia ኤክስፐርቶች ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡
- የ90 ኢንዲኬተር የመረጃ መሰብሰቢያ እና የሪፖርት ፎርማት እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡
- ከህዝብ ተወካዮች መ/ቤት ለቀረቡ 2 አስተያየቶች ግብረመልስ ተሰጥቷል፡፡

**የፋይናንስና ግዥና አስተዳደር**

የዘመነ የገቢና ክፍያ ስርዓት ማሳደግ

- የመንግስት የኤሌክትሮኒክ የክፍያ ስርዓትን መጨመር

የዘመነ የግዢ አገልግሎት ማስደግ

- በ6 ወር ሶስት ወር እና ወርሃዊ የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ ለማቅረብ 6 ታቅዶ6 ጊዜ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 100 % ነው፡፡
- በ6 ወር የሚቀርቡ የክፍያ ጥያቄዎችን በተፈቀደውና በቀረበው በጀት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ለመስጠት 6 ታቅዶ ማረጋገጥ ስራዎችን ተሰርቷል፡፡
- በ6 ወር በየወሩ ገቢ እና ወጪ መሰረት ያደረገ የበጀት መረጃ ምዝገባ ለማድረግ 6 ጊዜ ታቅዶ የ5 ወር ምዝገባ ተከናውኗል፡፡
- በ6 ወር የበጀት አጠቃቀም መረጃ ለስራ ክፍሎች በየወሩ ለማድረስ 6 ጊዜ ታቅዶ 6 የተዘጋጀ ሲሆን አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡

**የመንግስት የኤሌክትሮኒክ የክፍያ ስርዓትን መጨመር**

- በ6 ወር ከእንስሳት እና ከዕፅዋት ዘርፍ የሚገኙ የአገልግሎት ገቢዎችን ብር 1,250,000. /አንድ ሚልዮን ሁለት መቶ ሀምሳ ሽህ/ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 2,224,738.76 ከዕቅዱ በላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡
- በ6 ወር በስራ ኃላፊዎች ተፈቅደው እና በጀታቸውን ተረጋግጠ የሚቀርቡ ክፍያዎች 100 % ከጥሬ ገንዘብ ንክኪ የጸዳ የኤልክትሮኒክ ክፍያ ለመፈጸም ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት 100 % ተከናውኗል፡፡
- በ6 ወር የተከፈሉ ቅድመ ክፍያዎችን በወቅቱ እንዲወራረዱ በተደረው ክትትል መሰረት 100 % ለማወራረድ ታቅዶ 97 % እንዲወራረድ ሆኗል፡፡
- ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀት እና ለገንዘብ ሚኒስቴር ለማቅረብ 5 ጊዜ ታቅዶ 3 ጊዜ የቀረበ ሲሆን አፈጻጸሙ 60 % ሆኗል፡፡ (ዝቅ ያለበት ምክንያት የቃሊቲ ሪፖረት አዲስ ሲስተም የገባ ስለሆነ በመዘግየቱ ነው)፡፡

- ከተለያዩ ግዥዎችን የሚሰበሰቡ የተጨማሪ እሴት ታክስና ዊዝሆልድ የተቀነሱ (የተሰበሰቡ) ክፍያዎችን በማጣራትና በማደራጀት በወቅቱ 1,263,998.74 ገቢ ለማድረግ ችለናል፡፡
- በ6 ወር ከሚሌ ኳራንቲን ጣብያ የአገልግሎት ክፍያ ብር 157,415,845.57 የተሰበሰበ ሲሆን ለባለሙብቱ እስከ ህዳር 30/2018 የተሰበሰበውን ተመላሽ ሆኖ ክፍያ ተፈጽሟል፡፡
- በኤሌክትሮኒክ እና በሃርድ ኮፒ ክፍያ የተፈጸመባቸው ሰነዶች ማደራጀትና በሰነድ ክፍል በአግባቡ ለመያዝ በታቀደው መሰረት ሙሉ ለሙሉ ተናውኗል፡፡

## የመንግስት የኤሌክትሮኒክ የግዥ ስርዓት ለመጨመር የተከናወኑ ዋናዋና ተግባራት

- የተቋሙን አመታዊ የግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት ማጸደቅና በድህረ ገጽ ይፋ ለማድረግ ታቅዶ በእቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡
- በ6 ወር ሁለት የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ አንድ የተሽከርካሪ የጨረታ እና አንድ የደንብ ልብስ በድምሩ ሁለት ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን በእቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡
- ግዥዎች በ electronic government procurement system በተሟላ መልኩ ለመተግበር ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ሙሉ ለሙሉ ተተግብሯል፡፡
- በ6 ወር 15 ውሎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ ነባር ውሎች የውል ማሻሻያ ማዘጋጀት እና አዲስ ውሎች ማዘጋጀት በድምር 18 ውሎች የተዘጋጀ ሲሆን አፈፃፀሙ 120 %ነው፡፡
- የተከናዎኑ ዝርዝር ግዥዎች ለዋና መ/ቤት እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የቢሮ ኪራይ በውል ማዘጋጀት፣ ማጸደቅና ለክፍያ ማዘጋጀት፣ ለነዳጅ ግዥ ፣የህንፃ ለጥገና አገልግሎት፣ የተሽከርካሪ ጎማና ባትሪ፣ መለዋወጫ ዕቃ ግዥ ፣ ለጽ/መሳሪያ እና ጽዳት፣ የስካነር፣ የህትመት ስራዎች ግዥ፣ ለኢንሹራንስ አገልግሎት፣ የተለያዩ አገልግሎት ግዥዎች፣ ያልተጠቀሱ ጥቃቅን የመስተንግዶ ግዥዎችን በ6 ወር ተከናውኗል፡፡
- የተቋሙን ግብአት አቅርቦት ለማሳደግ በዋጋ ማቅረብያ እና በማዕቀፍ የሚቀርቡ ግዥዎችን ለማከናወን ታቅዶ 61.2 % የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙን ዝቅ ያለበት ምክንያት የማዕቀፍ ግዥ የሚቀርቡ ግዥዎችን በተሟላ መልኩ ባለመቅረቡ ነው፡፡
- ውል የተገባላቸው የአገልግሎት እና የዕቃ ግዥ የውል ሰነድ በማዘጋጀት በማጸደቅ አፈፃፀሙ ክትትል ተደርጓል፡፡
- በእቅድ ያልተካተቱ ጥቃቅን ግዥዎች እና ከአንድ አቅራቢ የሚቀርቡ የዘይትና ቅባት እና አቢሲንያ ካርድ ግዥዎችን ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡
- በ6 ወር የሚያገለግሉ በማዕቀፍ ግዥ የሚቀርቡ ሶፍት፣ የእጅ እና የልብስ የንጽህና መጠበቅያ ሳሙና ግዥ ተፈጽሟል፡፡

- የተለያዩ ግዥዎችን ውል፣ የዋና መ/ቤት እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቢሮ ኪራይ ውል፣ የህትመት ውል፣ የህንፃ የጥገና ውል እና ሌሎች ተያያዥ ውሎችን ተፈፃሚነታቸውን ለመከታተል በተያዘው ዕቅድ መሰረት ተከናውኗል፡፡

## ከግኝትነና ከቅሬታ የጸዳ የአሠራር ሥርዓትን መዘርጋት

- የክፍያ እና የግዥ ሰነድ አፈፃፀም የአሰራር ስህተት እንዳይኖር ከመፈጸሙ በፊት ተጣርተው እንዲፈጸሙ እና ከግኝት የጸዳ እንዲሆን ክትትል ተደርጓል፡፡
- በሚቀርቡ የኦዲት ግኝቶች ላይ ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ በታቀደው መሰረት አንድ ጊዜ የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ በዕቅድ መሰረት ተከናውኗል፡፡

## የተሰጡ ስልጠናዎች

- በግማሽ አመቱ ለባለስልጣኑ ከፍተኛ አመራር፣ መሪ ስራ አስፈፃሚዎች፣ ስራ አስፈፃሚዎች፣ የማዕከላት ኃላፊዎች ፣ ቡድን መሪዎች ፣የግዥና ፋይናንስ ባለሙያዎች አዲሱ የመንግስት የግዥ አዋጅና መመሪያ (1333/2016 እና 1073/2017) በሁለት ጊዜ ለ110 ተሳታፊዎች የአንድ ቀን ግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል፡፡
- የዋና መ/ቤት የቢሮ ኪራይ ላይ የተደረገው ጭማሪ የገንዘብ ሚ/ር የኪራይ ተመኑ እንዲያጸድቅ ጥያቄ ማቅረብና የማጸደቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

## የንብረት አያያዝና አጠቃቀም ማሻሻል

- በዚህ 6 ወር ደንብ ልብስ የጽዳት ዕቃዎችና የጥገና ዕቃዎችና ሌሎች ጥቃቅን ግዥዎች ጥያቄ ተከናዉነዋል
- በዚህ 6 ወር ቋሚ ዕቃዎች፣አላቂ ዕቃዎች፣ቋሚ አላቂ ዕቃዎችን ወደ ንብረት ክፍል ሲመጡ በሲስተም ተረክበናል፡፡
- በዚህ 6 ወር ቋሚ ዕቃዎች፣አላቂ ዕቃዎች፣ቋሚ አላቂ ዕቃዎችን ወጭ እንዲሆኑ ሲፈቀድ በሲስተም ወጭ ተደርጓል፡፡
- በዚህ 6 ወር ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር በሲስተም የተሰጠ ሲሆን ዕቃዎች ላይ ግን አልተለጠፈም፡፡
- በዚህ 6 ወር መቀሌ እና ድሬድዋ ማዕከል ያሉ 86 ዓይነት ቋሚ ንብረቶችን ተመዝግበዉ ባለቤት እንዲኖራቸዉ ተፈርጓል፡፡

## የትራንስፖርት ሥምሪት እና ጥገና አገልሎት ሥራወች ማከናወን

- በዚህ 6 ወር ለኢንስፔክሽን ስራ፣ለመስክ ሰራ እና ለሰርቢስ አገልግሎት የተሰጠ ስምሪት የመስጠት ስራ ተሰርታል አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነዉ
- በዚህ 6 ወር ለ 26 መኪና ቦሎ (ዓመታዊ ምርመራ) የማሰራት ስራ ተከናዉኗል፡፡
- በዚህ 6 ወር 35 መኪና በአንድ ሊትር ነዳጅ የሚሄደዉን የኪሎሜትር ልኬት ተከናዉኗል፡፡
- በዚህ 6 ወር ለ25 ተሽከርካሪ በፊሊት ማኔጂመንት ሲስተም የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል፡፡
- በዚህ 6 ወር ለ25 ተሽከርካሪ በፊሊት ማኔጂመንት ሲስተም በሊትር የሚሄደዉ ኪሎሜትር የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል፡፡
- በዚህ 6 ወር ለ25 መኪኖች የስምሪት ጥያቄዎች በፊሊት ማኔጂመንት ሲስተም ለመስጠት የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል፡፡
- በዚህ 6 ወር ለ25 የሰርቪስና ጥገና ጥያቄዎች በፊሊት ማኔጂመንት ሲስተም ለማከናወን የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል፡፡
- በዚህ 6 ወር ለ25 መኪኖች አሽከርካሪዎች የህይወት ታርክ በፊሊት ማኔጂመንት ሲስተም ተመዝግቧል፡፡

**የጠቅላላ አገልግሎት ስራን ማከናወን**

- በዚህ 6 ወር የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ ተችላል አፈፃጸሙም 96% ነዉ
- በዚህ 6 ወር ቢሮ ሽግሽግ በሚደረግበት ወቅት ቋሚ ዕቃዎችን በባለ ሙያ በማስፈታት እና በማጓጓዝ እንዳይሰበሩ እና እንዳይበላሹ ስራ ተሰርቷል አፈፃጸሙም 80% ነዉ ፡፡
- በዚህ 6 ወር ምንም እንኳን በቂ የጥበቃ ሀይል ባይኖርም ባሉን የጥበቃ ሰራተኞች የጥበቃ ስራዎችን በበአግባቡ ማከናወን ተችሏል አፈፃጸሙም100% ነዉ ፡፡
- በዚህ 6 ወር 2 ተጨማሪ የጽዳት ሰራተኞች ስለተቀጠሩ 100% ማከናዎን ተችላል ፡፡
- በዚህ 6 ወር የፎቶ ኮፒ ስራዎች ተከናዉነዋል አፈፃፀሙም 100% ፡፡

**የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል**

**የመረጃ ቋት ማደራጀት**

- በዚህ 6ወር ክላውድ የመረጃ ማጋሪያ እና ማከማቻ ሲስተም ማዘጋጀት ከኢትዮቴሌኮም የክላውድ ስቶሬጅ የመረጃ ማጋሪያ ስራ ተሰርቷል፡፡ 40% ታቅዶ 35% ተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 87.5 % ነው፡፡
- በዚህ 6ወር የባክአፕ ሲስተም ማዘጋጀት በባለስልጣኑ ለለሙ የኢፋይቶ እና የስጋ ኢንስፔክሽን ሲስተሞች የአውቶማቲክ ባክአፕ ስራ የተሰራ ሲሆን 50 % ታቅዶ 48% ተከናዉኗል አፈጻጸሙ 96 % ነው፡፡

➢ በዚህ 6ወር የመረጃ ደህንነት ሲስተም መዘርጋት በባለስልጣኑ ለሰሙ ሲስተሞች እና ለባለስልጣኑ የዌብሳይትና ኢሜይል የሴኩሪቲ (SSL Certificate) ስራ ተሰርቷል፡፡ 50% ታቅዶ 50% ተከናውናል አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡

**ወረቀት አልባ አሰራርን መተግበር**

➢ በዚህ 6ወር ማንዋል አገልግሎቶችን ወደ ኢሰርቪስ እና አንድ መስኮት ስርአት ማስገባት ወደ ኢሰርቪስ እና አንድ መስኮት እንዲገቡ የተጠየቁ አገልግሎቶች እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን፦
  - ✓ የእንስሳት መኖ ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈጻሚን 7 አገልግሎቶችን ወደ ኢ-ሰርቪስ በማስገባት ስልጠና በመስጠት ስራ ማስጀመር ተችሏል፡፡
  - ✓ የእንስሳት ኳራንቲን መሪ ስራ አስፈጻሚ 4 አገልግሎቶችን ወደ ኢ-ሰርቪስ ማስገባት የተቻለ ሲሆን ስራ ለማስጀመር ለባለሙያዎች የሲስተም ስልጠና ለመስጠት በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡50% ታቅዶ 48% ተከናውኗል፡ በመሆኑም አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡

➢ በዚህ 6ወር በመልማት ላይ ያለውን የephyto ሲስተም እንዲጠናቀቅ ማድረግ የephyto ሲስተም የመጀመሪያው ፌዝ የተጠናቀቀ ሲሆን ወደ ትግበራ በመግባት ላይ ይገኛል፡፡ ሌሎች ቀሪ ስራዎችም በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡የታቀደው 100% ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡

➢ በዚህ 6ወር በመልማት ላይ ያለውን የዘር ሰርቲፊኬሽንና ትራኪንግ ሲስተም እንዲጠናቀቅ ማድረግ ሲስተሙን የመገምገምና ሪፖርት የማቅረብ ስራ፡ እንዲሁም ኮድ የመሞከር ስራ ተጠናቆ የማሻሻያ ግንባታ ፕሮፖሳል ተዘጋጅቶ ቀርቧል እቅድ 50% ታቅዶ 45% ተከናዉኛል አፈጻጸሙ 90% ነው፡፡

➢ በዚህ 6ወር በመልማት ላይ ያለውን የስጋ ኤክስፖርት ኢንስፔክሽን ሲስተም እንዲጠናቀቅ ማድረግ የማልማቱና ቴስቲንግ ስራ ተጠናቆ ለሁሉም ቁራ ባለሙያዎች የሁለት ዙር ስልጠና ተሰጥቶ ፡ የዩዘር አካውንት ተፈጥሮ ወደ ተግበራ ተገብቷል፡፡ ከታቀደው 100% ሙሉ በሙሉ ተከናዉናል  አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡

➢ በዚህ 6ወር የተሽከርካሪ አስተዳደር ሲስተም መዘርጋት ሲስተሙ ተግባራዊ የተደረገ እና ዳታ ማለትም የተቋሙን ሙሉ ተሽከርካሪ እና ሰራተኛ ወደ ሲስተሙ የማስገባት ስራ የተከናወነ ሲሆን የተጠቃሚዎች ስልጠና TOR ጽድቆ ስልጠና ለመስጠትና ሙሉ በሙሉ በሲስተሙ ለመገልገል በዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡ 100% ታቅዶ 98% ተከናውኗል፡፡አፈጻጸም 98% ነው፡፡

**በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ኦቶሜት ማድረግ**

➢ በዚህ 6 ወር አሁን ያለውን ዌብሳይት እንደገና መገንባትና ማሻሻል አሁን ያለው ዌብሳይት ላይ አዳዲስ የማሻሻያ ስራ ማለትም ሜኑ መጨመርና ማስተካከል፡ ለኮምኒኬሽን ክፍል ዩዘር በመፍጠርና ግንዛቤ በማስጨበጥ መረጃዎችን ፖስት እንዲያደርጉ የማስቻል ስራ ተሰርቷል

እንደአዲስ ለማልማትና ዘመናዊና ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ ፕሮፖዛል በማዘጋጀትና በማጸደቅ በጀት የማፈላለግ ስራ እየተሰራ ይገኛል። 50% ታቅዶ 45% ተከናዉኗል አፈጻጸሙ 90% ሆኗል።

- በዚህ 6ወር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ልውውጥና አያያዝ ስርዓት ማሳደግ የከስተም (Custom) አንድ መስኮት አገልግሎት ከኢንተርኔት ወደ ቪፒኤን (VPN) እንዲሆን ስለተባለ መስመሩን አስገብተን በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።በማእከላትና በጣቢያዎች የኔትዎርክና የዳታ ሼሪንግ ስራ የተሰራ ሲሆን፥በመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለ2 ቢሮዎች ኔትዎርክ ዝርጋታ፡ በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የኔትዎርክና ፕሪንተር ሼሪንግ፡ በጉርድ ሾላ ለሚገኘው ማዕከላት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እና ላብራቶሪ አዲስ የኢንተርኔት መስመር ዝርጋታ፡ የፕሪንተር ሼሪንግ እና ዋይፋይ ገጠማ ስራ ተከናውኗል። 50% ታቅዶ 49% ተከናውናል አፈጻጸሙ 98% ሆኗል።
- በዚህ 6ወር የኤሌክትሮኒክና ኦንላይን ስርአቶችን ማስተዳደር የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶች ሳይቆራረጡ አገልግሎት እንዲሰጡ፡ የተጠቃሚዎችን አካውንት የማስተዳደር ስራ ተሰርቷል።
- በዚህ 6ወር የኢፍሚስ፣ የሰው ሀብት አስተዳደር እና ኢጂፒ፡ ኢሰርቪስ እና ኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት ሲስተሞች ላይ በአጠቃላይ የተረሳ ፓስዎርድ መቀየር፣ የስራ ድርሻ መቀየር፣ አዳዲስ አካውንቶችን መክፈት፣ በአጠቃላይ የመጡ የድጋፍ 45 ጥያቄዎች ሁሉም ተስተናግደዋል። ከታቀደው 100% በሙሉ በመከናወኑ አፈጻጸሙ 100% ነው።
- በዚህ 6ወር የሲስተም አስተዳደርና ድጋፍ ስራ ማከናወን በቢሮ ሽግሽግ ምክንያት አዲስ የኔትወርክ ዝርጋታ፣ ዴስክቶ፣ ላፕቶፕ እና ፕሪንተር ጥገና በአጠቃላይ 75 ጥገናዎች በግማሽ አመቱ ተደርጓል።ኮምፒተሮቻቸው ለመክፈት እና ለመጠቀም በጣም ይዘገዩ የነበሩ የ35 ባለሙያዎች ኮምፒተሮች RAM ግዥ ተፈጽሞላቸው ጥገና ተደርጎላቸው በጥሩ ሁኔታ ማስጠቀም ተችሏል።
- በ5 ሚልዮን ኮደርስ ኢኒሺየቲቭ ስልጠና ለ42 ሰራተኞች የመመዝገብና የመፈተን ድጋፍ ተደርጓል፡፡በአጠቃላይ 405 ሰራተኞች ሰርተፊኬት ወስደዋል። በመሆኑም የመጡ የድጋፍ ጥያቄዎች የተስተናገዱ በመሆናቸው አፈጻጸሙ 100% ነው።

## ተቋማዊ ለውጥ ሥራዎች ማሳደግ

የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ

- በ6 ወር ከውጭ እና ከውስጥ ተገልጋዮች ሊነሱ የሚችሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መለየት የሚያስችል መረጃ መሰብሰብ ተፈጻሚነቱን መከታተል ለ2 ጊዜ ለማከናወን የታቀደ ሲሆን በዋናው መ/ቤት የሚገኙ የሥራ ክፍሎች እና በኢትየጵያ ግብርና ባለስልጣን ምስራቅ ማዕከል ድሬደዋ ጣቢያ መረጃ የማሰባሰብ ስራ ተሰርቱዋል። አፈጻጸሙ 100 ፐርሰንት ነው።

- በ6 ወር ከውጭ እና ከውስጥ ተገልጋዮች የተሰበሰበውን መረጃ በመገምገም ፣ አንድ ሰነድ ማዘጋጀት የተሰበሰበውን መረጃ በመገምገም አንድ ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን ግብረመልስ በቃል ተሰጥቱዋል ሆኖም ተጨማሪ ቦታዎችን በማካተት አጠቃለን ለማቅረብ እየሰራን እንገኛለን። አፈጻጸሙ 100 ፐርሰንት ነው።

**በተቋሙ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መፍታት**

- ለውስጥ እና ለውጭ ተገልጋዮች የመልካም አስተዳደር አተገባበር ፣የቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብ እና አፈታት ሥርዓት ማሳወቅ በ6ወር በቁጥር አንድ ጊዜ ለማሳወቅ የታቀደ ሲሆን በተያዘው ዕቅድ መሠረት በጽሁፍ የማሳወቅ ሥራ ተሰርቱዋል አፈጻጸሙ 80 % ነው።
- ከውስጥና ከውጭ ተገልጋዮች የቀረቡ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች በሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች በኩል ምላሽ እንዲሰጥ የማድረግ ስራ ተሰርቱዋል። በ6 ወር የጎላ ከውጭም ሆነ ከውስጥ ተገልጋዮች የቀረበ ቅሬታ እና አቤቱታ የለም ።
- ለስራ አመቺ የሆኑ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለሌሎች ማስተላለፍ የሪፎርም ታስክ ፎርስ አስተባባሪ ጋር በጋራ በመሆን ኪው አር ተገልጋዮች ስለ አገልግሎት አሰጣጣችን በቴሌግራም አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል በወረቀት ከቀረበው ስኮር ካርድ በተጨማሪ ለአሰራር የሚያመች አዘጋጅተናል።

**የተገልጋዮች ቻርተር እና ተቋማዊ ካይዘን ሥርዓት መተግበር**

- ቻርተሩን ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ማጸደቅ የተገልጋዮች ቻርተር ለኢፌዲሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እንዲመዘገብልን የላክን ሲሆን ተቀባይነት አግኝቶ ቁጥር ተሰጥቶ ተመዝግቦልን ስራ ላይ ውሉዋል አፈጻጸሙ 100 % ነው።
- የተዘጋጀውን የዜጎች ቻርተር በስራ ላይ ማዋል ቻርተሩ በስራ ላይ እንዲውል በ6 ወር የታቀደ ሲሆን በተያዘው እቅድ መሰረት ተግባራዊ ተደርጉዋል አፈጻጸሙ100 %ነው።
- ቻርተሩን ማሳተም ማሰራጨት የቻርተሩ ስራ ተጠናቆ እና ማተሚያ ድርጅት ተለይቶ አንድ እትም ህትመቱን የሚያዘጋጀው ድርጅት አዘጋጅቶ ተቀባይነት አግኝቶ የሚፈለገውን ቁጥር ለማሳተም በመነጋገር ላይ እያለን በሌላ የአሰራር ስርዓት እንደሚተካ በኢፌዲሪ ስለታዘዘ የህትመቱ ስራ እንዲቋረጥ ተደርጉዋል ሆኖም አዲሱ አሰራር ትግባራዊ እስኪሆን ለስራ ክፍሎች ያሰራጨን ስለሆነ በስራ ላይ ይቀጥላል።
- ከካይዘን ኢንስቲትዩት ጋር ስምምነት ሰነድ በመፈራረም ካይዘንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል እቅድ ማዘጋጀት እና ተግባራዊነቱን መከታተል፡- ከኢንስቲትዩቱ ጋር በጋራ ለመሥራ የሚያስችል ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን ሆኖም ቀደም ሲል የተሰጠውን ስልጠና

መሰረት በማድረግ ወደ ስራ እንዲገባ በአመራር በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት በቢሮ ሽግሽግ ምክንያት በ6 ወራት (በግማሽ) አመቱ በርካታ የማስተካከያ ስራ ተሰርቱዋል፡፡

- ✓ የቢሮ አመላካች በተናጠል ለስራ ክፍሎች በቁጥር 18
- ✓ በወለል ላይ የስራ ክፍሎች አመላካች በጥቅል በቁጥር 5
- ✓ አቅጣጫ ጠቋሚ ቢል ቦርድ በቁጥር 2
- ✓ የጠረጴዛ ስም እና የስራ ድርሻ አመላካች በቁጥር 22 ተዘጋጅቶ ለሰራተኞች ተሰጥቱዋል፡፡

- ✓ በተጨማሪም የተገልጋዮች ቻርተር ተቀይሮ በአዲስ የአሰራር ስርአት እንዲተካ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ስቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አቅጣጫ በማስቀመጡ ወደስራ ተገብቷል
- ✓ የአገልግሎት ስነ ምድብ፣ የአገልግሎት ፍሰት ማፕ ፣የአገልግሎት ስታንዳርድ፣ እና ሰርቪስ ካታሎግ ሁሉንም መሪ ስራ አስፈጻሚች፣ዴስክ ሀላፊዎች እና የሪፎርም ቲሙን ያካተተ ስልጠና ተሰጥቶ በስራው ላይ የሚመለከታቸው አላማ እፈጻሚዎች እና የዴስክ ኃላፊዎች ያካተተ 4 ሰነድ ተዘጋጅቶ ለግብርና ሚኒስቴር እና ለኮሚሽኑ ተልኩዋል፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ከላይ በተገለጸው ርእሶች ላይ ለዋናው መቤ/ት ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቱዋል፡፡
- ✓ ለብቃት ማረጋገጫ ምዘና የሚረዳ 12 የቴክኒካል ብቃት አሀዶች እና 15ቱ የባህሪ ብቃት አሀዶች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በቪዲዮ ስልጠና ተሰጥቱዋል፡፡
- ✓ ማንኛውም ሰራተኛ የለውጥ መሳሪያዎችን እንዲጠቀም ድጋፍና ክትትል ማድረግ በእቅዱ መሰረት ሰራተኞው የለውጥ መሳሪያዎችን እንዲጠቀም ድጋፍና ክትትል ተደርጉዋል፡፡ አፈጻጸሙ 100 ፐርሰንት ነው፡፡
- ✓ በ6ወር ክትትል እና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ተጨማሪ መታወቂያ በቁጥር 25 እና ባጅ 30 ተዘጋጅቶ ለሰራተኞች ተሰጥቱዋል፡፡

**ተግባራዊ የተደረገ የህግ ማዕቀፍ**

በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ህጋዊ አስተያየት መስጠት

ባለፉት ስድስት ወራት በድምሩ 11 ለሚሆኑ ባለስልጣኑን ለሚመለከቱ የህግ ጥያቄዎች ህጋዊ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ከነዚህ መካከል በአንድ ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግ/ማ ላይ ፣በዋና መስሪያ ቤት የቢሮ/ህንፃ ኪራይ ውል ላይ የተሰጠ የሕግ አስተያየት ፣የትምህርት ስልጠና የውል ማቋረጥ ጥያቄ ፣ወደ አገር ውስጥ ስለገባ ሕገ ወጥ የመኖ ግብዓት ለቀረበ ጥያቄ ፣በትምህርት ስልጠና ወቅት የጥናትና ምርምር ክፍያ ጥያቄ ላይ፣ ከአንድ ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግ/ማ ለቀረበ ቅሬታ

መጠናቀቅ ከሚገባው ጊዜ በላይ ስለቆየ የትምህርት ስልጠናና ስለተቋረጠ የትምህርት ስልጠና ጉዳይ ላይ የሕግ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

ህጋዊነቱን ጠብቀው የተዘጋጁና ለቁጥጥር ተግባሩ የሚያግዙ አዋጅ፣ደንብ እና መመሪያ

| | |
|---|---|
| 1. ሜካናይዜሽን መሪ ሥራ አስፈፃሚ | የምርምር አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ መመሪያ ዝግጅት |
| 2. የእንስሳት መኖ ሬጉላቶሪ | የመኖ ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ማሻሻያ ዝግጅት |
| 3. የእንስሳት መድሀኒት ሬጉላቶሪ | የአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ መመሪያ ዝግጅት |
| 4. የእንስሳት መድሀኒት ሬጉላቶሪ | የመድሃኒት ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ መመሪያ ዝግጅት |
| 5. የእንስሳት መድሀኒት ሬጉላቶሪ | አዋጅ ቁጥር 728/2014 ማሻሻያ ዝግጅት |
| 6. የእንስሳት ኳራንታይን ሬጉላቶሪ | የእንስሳት ኳራንታይን ቁጥጥር መመሪያ ዝግጅት |
| 7. ፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ሬጉላቶሪ | ሥነ-ህይወታዊ ተባይ መከላከያ መመሪያ ዝግጅት |
| 8. ፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ሬጉላቶሪ | የፀረ-ተባይ ተቋማት ኢንስፔክሽን መመሪያ ዝግጅት |
| 9. ፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ሬጉላቶሪ | የማዳበሪያና የአፈር ጤንነት እና ግብይት አዋጅ ዝግጅት |

| | |
|---|---|
| 10. | የአገልግሎት ክፍያ ደንብ ዝግጅት |

- በ6 ወር ዉስጥ የሕግ ቅርፅ እና ይዘት ኖሮአቸው ዝግጅታቸውን የጨረሱ አዋጆች ደንቦች መመሪያዎች አጠናቆ ለሚመለከተው አካል እንዲፀድቅ መከታተል፤
    - የእፅዋት ጥበቃና ኳራንቲን አዋጅ ጸድቋል፤
    - ሁለት የዘር መመሪያዎች ፀድቀዋል፤
- በ6 ወር ዉስጥ ተዘጋጅተው በሚቀርቡ ውሎች እና ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሌሎች የውጪ አካላት ጋር የትብብር ወይም የመግባቢያ ስምምነቶች ተዘጋጅቶ በሚቀርበው ረቂቅ ሰነድ ላይ የሕግ አስተያየት መስጠት፤
    - ሰሜን ኢትዮጵያ ሰሜን ማዕከል የቢሮ ኪራይ ረቂቅ ውል ላይ አስተያየት
    - የጎንደር እፅዋት ኳራንቲን ጣቢያ ረቂቅ የቢሮ ኪራይ ውል ላይ አስተያየት መስጠት
    - በተዘጋጀ የውል ስምምነት ረቂቅ ላይ የሕግ አስተያየት መስጠት
    - በማዕከሉ በኩል በተዘጋጀ የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት የውል ስምምነት ላይ አስተያየት መስጠት
    - የህትመት ሥራ ውል ዝግጅት ላይ የሕግ አስተያየት መስጠት
    - የፓርትሽን የግንባታ ሥራ የውል ዝግጅት ላይ የሕግ አስተያየት
    - የትምህርት ስልጠና የውል ማሻሻያ (ማራዘሚያ) ዝግጅት ላይ አስተያየት ማቅረብ
    - በማዕከሉ በኩል ለቀረበ የጀነሬተር ጥገና የአገልግሎት ግዥ የውል ረቂቅ አስተያየት
    - የባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት የቢሮ ኪራይ የውል ማሻሻያ ላይ አስተያየት መስጠት
    - ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በመተባበር ትምህርታዊ አምድ ለማዘጋጀት በቀረበ ውል ላይ አስተያየት

**በ6 ወር ዉስጥ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱን ወክሎ የሕግ ክርክር ማካሄድ**

- ✓ በ6 ወር ዉስጥ አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም መመሪያዎችን፤ ደንቦችን በመተላለፍ ወይም በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ላይ የሚፈፀሙ የፍትሀ-ብሄር ግድፈት በሚኖርበት ጊዜ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱን ወክሎ በ3 ሶስት ጉዳዮች ላይ ክርክር ተደርጓል፡፡ክርክሮች የተደረጉት በሲቪል ሰርቪስ ችሎት፣መደበኛ ፍርድ ቤት- እንዲሁም አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡

**በ6 ወር ዉስጥ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች በሚኖሩበት ጊዜ ውሳኔዎቹን በአግባቡ ተከታትሎ ማስፈጸም**

በዚህ ጉዳይ 4 ጉዳዮች ውሳኔ ተሰጥቶባቸው የአፈፃፀም መዝገብ ተከፍቷል፡፡

**በ6 ወር ውስጥ ሕግ የማስከበር (ማፅዳት) የተከናወነባቸው ቦታዎች**

- 3.ድሬደዋ 2. ሞያሌ ኦሮሚያ 3. አዋሽ 4. ኮንሶ 5. ቡሌ ሆራ(ሀገረ ማሪያም) 6.አሰበ ተፈሪ (ጭሮ) 7. ሞያሌ ሱማሌ 8. ባቢሌ 9. ሐረር 10.ዲላ

- ✓ አሰበ ተፈሪ በዴሳ ወረዳ ላይ ሁለት የእንሰሳት መድኃኒቶች ቤቶች ደንብ እና መመሪያ ባለማክበር እንዲዘጉ (እንዲታሽጉ) ተደርገዋል፡፡
- ✓ ድሬደዋ ላይ አንድ ንግድ ቤት የንግድ ፍቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለማሳደሳቸው እንዲታሽግ ተደርጓል፡፡
- ✓ ጭሮ ላይ በመንገድ / በጎዳና ሲነግዱ የተገኙ ነጋዴዎች በመገኘታቸው እርምጃ እንዲወሰድባቸው ክስ እንዲመሰረትባቸው ሆኗል፡፡
- ✓ በ6 ወር ዉስጥ ግንዛቤ የማስጨበጥ የተከናወነባቸው መድረኮች
- ✓ አዳማ ላይ ሁለት መድረክ
- ✓ ድሬደዋ
- ✓ ሐዋሳ
- ✓ በ6 ወር ዉስጥ የቁጥጥር ሥራ ለሚያከናውኑ የመ/ቤቱ ባለሙያዎች የሕግ ድጋፍ መስጠት
- ✓ ለፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ሬጉላቶሪ የፍሳሽ ማዳበሪያ በተመለከተ የህግ ክትትልና ድጋፍ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡
- ✓ ወደ አገር ውስጥ በሕገ-ወጥ መንገድ ገብቶ ክስ ተመስርቶበት የነበረ የኬሚካል ምርት ክሱ የተቋረጠ ቢሆንም እንደገና እንዲመረመር ተደርጎ እንዲቀጥል በማድረግ ለፌደራል ፖሊስ እንዲተላለፍ ሆኗል፡፡
- ✓ በ6 ወር ዉስጥ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ከሕግ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶችና ውይይቶች ላይ በመሳተፍ ለቁጥጥር ተግባሩ የሚሆን የሕግ ነክ ግብዓት 100 % ተከናዉኗል ፡፡ በባለድርሻ አካላት በተዘጋጁ 6 የሕግ ረቂቅ የተመለከቱ ውይይቶች ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡

| *የረቂቁ ስያሜ* | *አስተባባሪው አካል* |
|---|---|
| *1. የመልክአ ምድራዊ አመልካች ምርቶች ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ* | *አእምሯዊ ባለስልጣን* |
| *2. ዲጅታል ሲስተም ስልጠና* | *ፍትህ ሚኒስቴር* |
| *3. አዋጅ 1183/12* | *ፍትህ ሚኒስቴር* |

| | |
|---|---|
| *4. የአካባቢ ጥበቃ ረቂቅ* | *የተወካዮች ም/ቤት ያዘጋጀው የህዝብ መድረክ* |
| *5. ግብርና ሚኒስቴር* | *የእንሰሳት ውጤቶች ግብይት አዋጅ* |
| 6. የባለብዙ ተዋናይን ኤክስቴሽን አዋጅ | ግብርና ሚኒስቴር |

## አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት

*የገፅ ለገፅ፤ የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ*

- ✓ በ6 ወር ዉስጥ በመረጃ ዴስክ አማካኝነት የውስጥና የውጭ ደንበኞችን በመልካም መስተንግዶ ተቀብሎ አስፈላጊ መረጃዎችን 100% ለመስጠት ታቅዶ 100% ተከናውኗል፡፡
- ✓ በ6 ወር ዉስጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ስምምነት በመፍጠር የተቋሙን የስራ እንቅስቃሴ ሊያሳይ የሚችል አንድ የዶክመንተሪ ፊልም ለማሰራት ታቅዶ ከግብርና ሚ/ር ህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ከኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ማህበር ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ ብሔራዊ የዕፅዋት ጤና ጥበቃ (ePhyto System) ስረዓት ላይ ያተኮረ ኮንፈረንስ ላይ የሚቀርብ አንድ ዶክመንተሪ ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡
- ✓ በ6 ወር ዉስጥ ከተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚመጡ ረቂቅ መመሪያዎች ላይ ከባለድርሻ አካላት ሀሳብ ለመሰብሰብ እንዲቻል በፌደራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 8 መሠረት ማስታወቂያ አዘጋጅቶ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲወጣ ለማድረግ ታቅዶ ሁለት ጊዜ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡
- ✓ በ6 ወር ዉስጥ በተቋሙ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የለውጥ እንቅስቃሴ ለማሳየት 2 ጊዜ ጋዜጣዊ መግለጫ 2 ጊዜ ብሮሸር አዘጋጅቶ ማሰራጨት 3 ጊዜ የዜና መጽሔት አዘጋጅቶ ማሰራጨት በዌብ ሳይት ላይ በመጫን ስኬቶችን የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡
- ✓ አዋጆችን፣ ደንቦችንና እና መመሪያዎችን 100% ለማሰራጨት ታቅዶ የእንስሳት መድሀኒት ምዝገባ መመሪያ፣ 200 ኮፒ፤ 5 ጋይድ ላይን እያንዳንዳቸው ሃምሳ ሃምሳ ኮፒ፤ ብሮሸር 2000 ኮፒ በድምሩ 2450 ኮፒ ተሰራጭቷል፡፡

## ሶሻል ሚዲያውን አይቶ ወደ ተግባር እንዲገባ የሚያስችል መልእክት መተላለፉ

- ✓ በ6 ወር ጥራት ያላቸው መልዕክቶችን በማዘጋጀት በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች( በቴሌግራም፤ በፌስቡክ፤መረጃዎችን 100% ለተገልጋይ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ ባሉን ማህበራዊ ሚዲያዎች (በፌስ ቡክና በቴሌግራም ብቻ ወቅታዊ መረጃዎችን 100%

በመጫን ለተገልጋይ ተደራሽ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፣ዩቲዩብ የተከፈተ ቢሆንም የካሜራ ባለሙያ ባለመኖሩ መጠቀም አልተቻለም)

- ✓ በ6 ወር የስራ ክፍሉ ከሌሎች ስራ አስፈጻሚዎች ጋር የተቀናጀ፣ የተሳለጠና ወጥነት ያለው የመረጃ ልውውጥና የኮሙኒኬሽን ስርዓት እንዲኖር የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው፡፡

## ሁነቶችን በማደራጀት ስኬቶችን ማስታዋወቅና መግባባትን መፍጠር

- ✓ በ6 ወር በተቋሙ የሚከናወኑ የተለያዩ ሁነቶችን ሕብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲያገኝ የማድረግ ሥራ 100% ለመሥራት ታቅዶ በተለያዩ የስልጠናና የውይይት መድረኮች በበላይነት የመምራት ስራ ተሰርቷል፡፡
- ✓ በ6 ወር በ3 ጣቢያዎች ላይ በአካል በመገኘት የሕዝብ ግንኙነት ስራዎችን ለመስራትና ከመረጃ አያያዝና አጠቃቀም አኳያ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ሞጆ፤ አዳማና ሀዋሳ ላይ በመገኘት ድጋፍ የማድረግ ስራ ተሰርቷል
- ✓ በ6 ወር የሚዲያ አካላት ስለ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ እየተዘገቡ የሚወጡትን በየዕለቱ በመከታተልና ሞኒተር በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት በማድረግ ለአሉታዊ ጽሁፎች አስፈላጊውን የማስተካከያ መረጃ መስጠት ወይም እንዲሰጥ ለማድረግ ታቅዶ 100% ተከናውኗል፡፡
- ✓

## ስነ ምግባርና የፀረ ሙስና

የተከናወኑ የሥነ-ምግባር ግንባታ ውጤታማነት የማሳደግ ሥራዎች

- ✓ በ6ወር በኤሌክትሮኒክስ እና ማህበራዊ ሚድያ (ቴሌግራም፤ፌስክ፤ኢሜል---ወዘተ) የስነ-ምግባር መልክቶችን ተላልፋል አፈፃፀሙም 100 ነዉ %፡፡
- ✓ በ6ወር ርበባለስልጣን መስሪቤት የምስራቅ ጣቢያ የሚገኙ 53 ሰራተኞች በስነ-ምግባር ዙሪያ ላ የግንዛቤ መስጨበጫ ስልጠና ( የሥነ-ምግባር ምንነት ፤ የሙስና ወንጀል ምንነ የሙስና ዓይነቶች ፤የሙስና ወንጀል ልዩ ባህሪያትና በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች) ተሰጥቷል፡፡
- ✓ አዳማ፤ቢሾፍቱ ፤ዱከም ሞጆ፤ መተሃራ ለሚገኙ ለመስሪያቤተችን በቁጥር 65 ለሚደርሱ ሰራተኞች በመስሪቤቱ በስነ-ምግባር መመሪያ ላይ የግንዛቤ መስጨበጫ ስልጠና አዳማ ከተማ ላይ ተሰጥቷል፡፡
- ✓ ሃዋሳ ከተማ ለሚገኙ ለመስሪያቤታች ሰራተኞች በተቋማችን የስነ-ምግባር መመሪ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- ✓ አለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን አንደ ግብርና ዘርፍ በጋራ አስሩም ተቋማት በግበርና ምርመር ኢንስትቲዩት አክብረናል፡፡
- ✓ በ6 ወር በሀብት ማሳወቅ ምዝገባ በአዋጅ ቁጥር 668\2002 መሰረት መስሪያ ቤታችን አዲስ እና እድሳት ምዝገባ በዲጀታል ሲስታም 38 ሰራተኞች በሃርድ ኮፒ 3 ከፍተኛ አመራር በአጠቃለይ 41 ሰራተኞች ሃብትና ንብረት አስመዝግበዋል፡፡

**የሙስና መረጃ አስተዳደር ውጤታማነትን ማረጋገጥ**

- ✓ በ6 ወር አስቸኳይ የሙስና መከላከል በሚል እቅድ ተይዞ የቀረበ ጥቆማ ብዛት ለ1 ሰዉ ይሄንንም ጥቆማ ከሶስት የስራ ክፍሎች(ከስነ-ምግባር፤ ከህግ፤ከተቋማዊ ለውጥ) በጋራ በመሆን ጥቆመውን በማጣራት ለሚመለከው አከል ተሰጥቷል፡፡
- ✓ በ6 ወር የሚመጡ የሙስና መረጃዎች ጥቆማዎች መቀበል መተንተን (በሚታዩበት ጊዜ) የቀረበ ጥቆማ አንድ ሲሆን ጥቆማው ተተንተኖ ለሚመለከተው አካል ቀርቧል፡፡

**ታቅደው ያልተከናወኑ ሥራዎች ከነምክንያታቸው**

- የማር እና ሥጋ ኬሚካል ቅሪት የምርመራ ሥራዎች በላቦራቶሪ መሳሪያዎች ብልሽት ምክንያት
- የምርመራ ስነ-ዘዴ ቅቡልነትና ተዓማኒነት ማረጋገጫ (Test method validation) ተግባራት ለማከናወን የሚያስፈልጉ የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት ግዥ መጓተትና ተደራራቢ ሥራዎች በሙብዛታቸው ምክንያት አልተሰራም፡፡
- የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ጥገና መለዋወጫዎች እና የጥገና አገልግሎት ግዥ በበጀት እጥረት ምክንያት አልተከናወኑም፡፡
- በዚህ ግማሽ ዓመት ለአንድ (1) የግብርና ምርምር/ኤክስቴንሽን/ ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ አልተከናወነም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የቁጥጥር ስራው ለማስጀመር የተዘጋጁ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያዎች ባለመጽደቃቸው ነው፡፡
- ከሬዲዮ ወይም ከቴሌቪዥን ጣቢያዎች ጋር ስምምነት በመፍጠር በ5 ቋንቋዎች ለህብረተሰቡ መረጃ ማድረስ ከበጀት ጋር በተያያዘ አልተከናወነም፡፡

## 6. የበጀት አጠቃቀም

| የበጀት ዓይነት | መለኪያ | ለ2018 | የ6 ወራት | አፈጻጸም |
|---|---|---|---|---|

| | | የተፈቀደ በጀት | | | | ከዓመቱ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንዉን | አፈጻጸም በመቶኛ | |
| መደበኛ | በብር | 312,944,341.64 | 151,109,606.28 | 150,208,567.50 | 99.4% | 48% |
| ድምር | | | | | | |

## 7. ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍ

ለክልሎች ድጋፍ ለመስጠት እንዲሁም አብሮ ለመስራት የሚያስችሉ በርካታ ክንውኖች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል

- ከግብርና ሚኒስትር ጋር በጋራ የምግብ ደህንነት እና ጥራት የማሰልጠኛ ማንዋል፣ ፐርዘንቴሽን እና ፋሲሊቴተር ጋይድላይን ተዘጋጅቶ ለክልል እና ለተመረጡ ባለሙያዎች በምግብ ጥራት እና ደህንነት ቁጥጥር ላይ ToT ሊሰጡ የሚችሉ 8 ባለሙያዎች ከባለስልጣን መስሪያቤቱ በተዘጋጀው ዶክመንት ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፣ ስልጠናም ተሰጥቷል፡፡

- ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለሁሉም ክልል ከቅርንጫፍ ማዕከላት የሬጉላቶሪ ኃላፊዎች ስለ ፍራፍሬ ችግኝ ጣቢያ እና የፍራፍሬ ችግኝ የጥራት ቁጥጥር መስፈርት ወይም ደረጃ ሰፋ ያለ አጠቃላይ ሀገራዊ የፍራፍሬ በተለይም የአቮካዶ ልማት እና ሀገራዊ ስትራቴጂ፣ ዋና ዋና የፍራፍሬ በሽታ ክስተትና መከላከያው ዘዴ፣ የክልሎች የፍራፍሬ ቁጥጥር ስራና ያጋጠማቸው ችግር፣ የፍራፍሬ ምርምር ያለበት ደረጃና የወደፊት አቅጣጫ፣ የተሻሻሉ ደረጃዎች ዙሪያ በሚመለከት በባለሙያዎች/ኃላፊዎች ከቀረቡ በኃላ ወይይትና የመስክ ምልከታ በማድረግ ለቀጣይ የስራ ክፍፍል ተደርጓል፡፡
- ለሲዳማና ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች የፍራፍሬ የችግኝ ጥራት ቁጥጥርን ስራን በሚመለከት በክልሉ ለሚገኙ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል፡
- ከአለም አቀፍ የዘር ጥራት ማህበር /ISTA/ አስራር ጋር በተገኘኘ የመጀመሪያው ዙር ከኦሮሚያ፣ ከአማራ፣ ከሲዳማ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ፣ ከደቡብ መህራብ ኢትዮጵያ፣ ከትግራይ እና ከማዕከላዊ ኢትዮጰያ ለተወጣጡ በቀጥታ ስራውን እየሰሩ ለሚገኙ

ባለሙያዎች በዘር ናሙና አወሳሰድ እና በመሰረታዊ የዘር ፍተሻ በላብራቶሪ ፓራሜትሮች ላይ ተግባር ተኮር ስልጠና በአንጋፋ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- የአትክልት ዘር በሽታዎችን የመለየት የቁጥጥር ስራ በሚመለከት በተመረጡ ሰብሎች ማለትም ቀይ ሽንኩርት፣ ነጭ ሽንኩርት እና በርበሬ ፌደራልን ጨምሮ ከ16 ማዕከላት ከተወጣጡ ባለሙያዎች በሁለት ዙር የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል፡፡
- በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ለሚገኙ የተመረጡ የምግብ ደህንነት ምርመራ እና የእጽዋት ዘር ጥራት ምርመራ ስራ ለሚሰሩ ላቦራቶሪዎች በቦታው በአካል በመገኘት በተለያዩ የምርመራ ዘዴዎች ላይ እና በላቦራቶሪ አስተዳደር ስርአት ላይ የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል፡
- ለስራ ክፍሉ ሰራተኞች በተለያዩ የምርመራ ዘዴዎች ላይ እና በISTA ፕሮፊሽንሲ ቴስት ናሙና አፈታተሽ ላይ የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከፌዴራል እና ከተለያዩ የክልል ግብርና ቢሮዎች እና የግብርና ግብዓቶች እና ምርት ቁጥጥር ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች ለተውጣጡ የእጽዋት ዘር የላቦራቶሪ አናሊስቶች እንዲሁም የስራ ሀላፊዎች በ6 ወሩ በሁለት ዙር የተለያዩ ስልጠናዎች (ማለትም፦ በውጤታማ የማሙና አወሳሰድ፣ በናሙና አዘገጃጀት፣ መሰረታዊ የማይክሮስኮፕ አጠቃቀም እና አያያዝ፣ የእጽዋት ዘር በሽታዎች ልየታ ላይ እንዲሁም በኳሊቲ ኮንትሮል እና በኳሊቲ አሹራንስ ላይ) በስራ ክፍሉ ተሰጥተዋል፡፡
- ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን በጋራ በእንስሳት ምርት ጥራት፣ጤንነትና ደህንነት ላይ ለሚሰሩ 65 ኢንስፔክተሮችና ሰርተፊኬሽን ባለሙያዎች የዓቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከኦሮሚያ የግብርና ግብአቶችና ምርት ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በመተባበር ለ60 ባለሙያዎችና የወተት አመራች ህብረት ስራ ተወካዮች በእንስሳት ምርት ጥራት ኢንስቴክሽን እና በሬጉላቶሪ ዙሪያ ያሉትን የህግ ማእቀፎት ለሁለት ቀናት ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናና ተሰጥቷል፡፡
- ከSNV Bridge+ ፕሮጀክት ጋር በመተባባር በሲዳማ እና ኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን የሚገኙ 45 የኮሜርሻል የወተት እርባታዎች ላይ የጥሬ ወተት እና የእንስሳት መኖ

ላይ በAflatoxin መበከል ጋር የተያያዘ የዳሰሳ ጥናት ተካሄዶ ከባለድሻ አካላት ጋር ውይይት በማካሄድ የጋራ ተደርጓል፡፡

- ከSNV Bridge+ ፕሮጀክት ጋር በመተባባር ኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አከባቢዎች የሚገኙ 14 የኮሜርሻል የወተት እርባታዎች ላይ የጥሬ ወተት የመድሀኒት ቅሪት ጋር የተያያዘ የዳሰሳ ጥናት ተካሄዷል፡፡
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእንስሳት ምርት ሬጉላቶሪ እና በሌሎች ምርቶች ዙሪያ ለመስራት የመግባቢያ ስምምነት ተፈርሟል፡
- ባለስልጣኑ እያከናወነ የሚገኘውን የቁጥጥር ስራ ወደ ክልሎች ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ ውይይት በባለስልጣኑ የእንስሳት መድሃኒት ሬጉላቶሪና በክልል ተቆጣጣሪ አካላት እንዲሁም ከተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር አውደ ጥናት በማድረግ በተለይም በእንስሳት መድሃኒት መላመድ፣ እንዳይገቡና ጥቅም ላይ እንዳይውሉ መታገድ ባለባቸው መድሃኒቶች ዙሪያ እንዲሁም እንደ ስጋና ወተት ባሉ የእንስሳት ተዋጽኦ (ውጤቶች) ላይ ጥራትና ደህንነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በሚያሳድሩ እንደ አፍላቶክሲን ያሉ የመኖ ጥራትና ደህንነትን ሊያበላሹ በሚችሉ የመኖ አከመቻቸት እና በመሳሰሉ ጉዳዮች እንዲሁም ለመድሃኒት ቁጥጥር ስራዎች እንቅፋት የሆኑ አሰራሮችንና ግንኙነትን ለማሻሻል የሚረዱ አሠራሮች ዙሪያ ምክክር ተደርጎ ሀሳብ ተሰብስቧል፡፡

## 8. በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች፣ የተወሰዱ እርምጃዎች እና በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገቡ መፍትሄዎች

- ✓ በጀት እጥረት
- ✓ የቢሮ ኪራይ መጨመር
- ✓ የተሽከርካሪ እጥረት
- ✓ ከፍተኛ የሆነ የሰው ሀይል እጥረት
- ✓ የእጽዋት ላቦራቶሪ ህንጻ ደረጃውን የጠበቀ አለመሆን

## የተወሰዱ እርምጃዎች እና በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገቡ መፍትሄዎች

- ✓ የበጀት ሽግሽግና ተጨማሪ በጀት ማስፈቀድ
- ✓ ሁለት ወለሎችን በመለቀቅና የቢሮ ሽግሽግ በማድረግ ችግሩን ለማቅለል ተሞክሯል፡፡
- ✓ ከግብርና ሚ/ር ተጨማሪ ተሽከርካሪ ለማግኘት ተችሏል
- ✓ ሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር በልዩ ሁኔታ ቅጥር እንዲፈቅድ ጥያቄ እየቀረበ ይገኛል፡፡
- ✓ የእጽዋት ላቦራቶሪ ህንጻ የማሻሻልና የማደስ ስራ በመከናወን ላይ ነው፤፤

### 9. ማጠቃለያ

ባለፉት ስድስት ወራት የባለስልጣኑ አፈጻጸም በጣም ጥሩ የነበረ ቢሆንም በተለይም ባለፉት ጊዜያት የታዩ ክፍተቶች ላይ በትኩረት መስራት ይህም ታቅደው ያልተከናወኑ ተግባራትን በቀጣዮቹ ሩብ ዓመታት ማከናወን ፣ እንዲሁም በተቻለ መጠን ወጪ ቆጣቢ የሆኑ የአሠራር ዘዴዎችን መጠቀም፣ ዲጂታላይዜሽንና አውቶሜሽን አሠራሮችን ማጠናከር እንደሚገባ ባለስልጣኑ ያምናል፡፡

## 11. የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2018 በጀት ዓመት የስድስት ወራት አፈፃፀም

| የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2018 ዕቅድ | የ2ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ2ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ6 ወር ዒላማ | የ6 ወር አፈፃፀም | የ6 ወር አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የግብርና ቁጥጥር ስራዎች | | | | | | | |
| ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ | | | | | | | |
| ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ | ቶን | 121,579.00 | 30,394.00 | 24,482.06 | 69,299.00 | 60,387.00 | 87.1 |
| ጥራቱ የተረጋገጠ የአፈር ማዳበሪያ | ቶን | 2,441,854.00 | 488,370.00 | 205,115.00 | 854,649.00 | 542,091.00 | 63.4 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 295 | 85 | 37 | 180.00 | 168.00 | 93.3 |
| በአከባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ | በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 2.00 | 2.00 | 100.0 |
| በመስክ ምርምር ፣ በዶዜር ግምገማ እና በቤተ-ሙከራ ፍቱንነቱ፣ ደህንነቱ ና ጥራቱ ተረጋግጦ የተመዘገበ ፀረ-ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ | በቁጥር | 445 | 130 | 189 | 235.00 | 337.00 | 143.4 |
| ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች | | | | | - | | |
| ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች | ሜ/ቶን | 960,000.00 | 240,000.00 | 243,220.00 | 480,000.00 | 422,755 | 88.1 |
| ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች | ሜ/ቶን | 65,000.00 | 16,250.00 | 83,051.00 | 32,500.00 | 123,704 | 380.6 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 680 | 169 | 54 | 340.00 | 170 | 50.0 |
| በላቦራቶሪ የጥራት ፍተሻ የተደረገላቸው የእጽዋት ዘር፣ እጽዋት ምርት እና የእጽዋት ውጤት ናሙናዎች | | | | | - | | |

| የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2018 ዕቅድ | የ2ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ2ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ6 ወር ዒላማ | የ6 ወር አፈፃፀም | የ6 ወር አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ጥራት በላቦራቶሪ ፍተሻ የተረጋገጠ ከውጭ ሀገር የገባ የእጽዋት ዘር ናሙና** | **ቁጥር** | 300 | 80 | 93 | 140.00 | 163.00 | 116.4 |
| ከክልል በሚመጡ የተለያዩ የሰብል/የአትክልት ዱፕሊኬት (Duplicate) ናሙናዎች ላይ የተከናወኑ የንጽጽር የላብራቶሪ ፍተሻ ስራዎች | ቁጥር | 40 | 10 | 18 | 20.00 | 18.00 | 90.0 |
| ጥራትና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች | ቁጥር | 20 | | | | | 100.0 |
| ጥራትና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች | ቁጥር | 20 | | 14 | - | | |
| **በምርምር ቀርበው በመስክ የተገመገሙ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎች** | **ቁጥር** | 120 | 60 | 41 | 70 | 75 | 107.0 |
| **በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ ከውጭ አገር የሚገባ ዘር መጠን** | **ኪ.ግ** | 38,308 | 150,000 | 139,531 | 250,000 | 222,632 | 91.0 |
| **ለዘር ስራ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች** | **ቁጥር** | 30 | 10 | 8 | 15 | 14 | 93.3 |
| ውጤታማነቱ፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ | | | | | - | | |
| ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ | በቁጥር | 10 | | | 1.00 | | |
| በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት | በቁጥር | 34 | 4 | 4 | 4.00 | 4.00 | 100.0 |
| ንዑስ ፕሮግራም፡- የእንስሳትና ከእንስሳት ጋር የተገናኙ የግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ቁጥጥር ማጠናከር | | | | | - | | |
| የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ | | | | | - | | |
| ደህንነቱ ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ስጋና ተረፈ ሥጋ | በቶን | 25,000 | 6,500 | 6,864 | 12,500.00 | 11,375.00 | 100.0 |

| የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2018 ዕቅድ | የ2ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ2ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ6 ወር ዒላማ | የ6 ወር አፈፃፀም | የ6 ወር አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የስጋና ተረፈ ስጋ አምራች ተቋማት | በቁጥር | 16 | 16 | 13 | 16.00 | 16.00 | 100.0 |
| ጥራቱና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ የተረጋገጠ የእንስሳት ምርት ናሙናዎች | በቁጥር | 730 | 183 | 314 | 363.00 | 393.00 | 100.0 |
| ለኮመርሻል የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ | በቁጥር | 91 | 45 | 25 | 45.00 | 45.00 | 0.0 |
| በእንስሳት ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 60 | 15 | 7 | 30.00 | 30.00 | 76.8 |
| በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች | | | | | - | | |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ የቁም እንስሳት | ቁጥር | 650,000 | 159,000 | 162543 | 306,085.00 | 306,085.00 | 100.0 |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ የለማ እንቁላል | በቁጥር | 573,000 | 140,000 | | 282,000.00 | | 0.0 |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ሰምና ማር | በቶን | 200 | 58 | 41.067 | 103.00 | 79.06 | 76.8 |
| ጥራቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ቆዳና ሌጦ | በቁጥር | 4,500,000 | 1,100,000 | 1,007,710 | 2,200,000.00 | 2,001,840.00 | 91.0 |
| ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል | በቁጥር | 738,492 | 185,246 | 666,028 | 369,246.00 | 1,775,681.00 | 480.9 |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ የተሻሻለ ዳልጋ ከብት | ቁጥር | 350 | 85 | 40 | 165.00 | 535.00 | 324.2 |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ አባላዘር | ዶዝ | 160,000 | 40,000 | 35,800 | 80,000.00 | 73,450.00 | 91.8 |
| ለቁም እንስሳት፣ የእንስሳት ምርቶች እና ለውጭ ንግድ የታቀዱ የእንስሳት ተረፈ ምርቶች ላይ ለመከናወን የተቀዱ ኢንስፔክሽን | ቁጥር | 70 | 17 | 19 | 33.00 | 37.00 | 112.1 |
| የእንስሳት ጤና እና የጥራት ደረጃዎችን የሚያሟሉ የላብራቶሪ ምርመራዎች ብዛት ከውጭ ለሚገቡ የእንስሳት ግብዓቶች (የአንድ ቀን ጫጩት፣የዘር ፈሳሽ ፣የለማ እንቁላል እና ጊደሮች) ብዛት | ቁጥር | 4,000 | 1200 | 1133 | 1,700.00 | 1,598.00 | 94.0 |

| የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2018 ዕቅድ | የ2ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ2ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ6 ወር ዒላማ | የ6 ወር አፈፃፀም | የ6 ወር አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ከዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና፣ ደህንነት እና የምግብ ደህንነት ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ የቁም እንስሳትን ወደ ውጭ ለመላክ የሚደረጉ የላብራቶሪ ምርመራዎች | በናሙና ቁጥር | 160,000 | 40,000 | 71,667 | 80,000.00 | 103,123.00 | 128.9 |
| ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት | | | | 0 | - | | |
| ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት | በቶን | 3,500 | 875 | 1030.2 | 1,750.00 | 2,195.09 | 99.7 |
| ተገምግሞ፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ የተመዘገበ የእንስሳት መድሃኒት | በቁጥር | 120 | 30 | 33 | 60.00 | 80.00 | 133.3 |
| የመድሃኒት ናሙዎችን ላይ የተካሄደ የጥራት፣ ደህንነት አና ፈዋሽነት የላቦራቶሪ ምርመራ | በቁጥር | 380 | 95 | 203 | 190.00 | 294.00 | 81.9 |
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት | በቁጥር | 410 | 268 | 258 | 339.00 | 321.00 | 115.9 |
| የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 682 | 171 | 186 | 341.00 | 340.00 | 88.0 |
| ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ | | | | | - | | |
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ መኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት | በቁጥር | 565 | 170 | 145 | 398.00 | 326.00 | 182.5 |
| ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ መኖ እና የመኖ ግብዓት | በቶን | 7000 | 2000 | 2512.876 | 3,500.00 | 4,055.00 | 115.9 |
| በእንስሳት መኖ እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 384 | 119 | 106 | 184.00 | 162.00 | 100.0 |
| ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ የተመረተ የተቀነባበረ መኖ | በቶን | 300,000 | 75,000 | 66,725 | 150,000.00 | 138,725.00 | 92.5 |
| የመኖ እና የመኖ ጥሬ ግብዓት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የጥራት እና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ | በቁጥር | 160 | 40 | 143 | 80.00 | 146.00 | 182.5 |

| የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2018 ዕቅድ | የ2ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ2ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ6 ወር ዒላማ | የ6 ወር አፈፃፀም | የ6 ወር አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የዕጽዋት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት | | | | | - | | |
| የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ ሥራዎችን በማጠናከር እውቅና የተገኘባቸውን 13 የላቦራቶሪ ምርመራ ሥራዎችን ማስቀጠል | በመቶኛ | 100% | 25% | 25% | 50% | 50% | 100.0 |